Ethiopian Economic Association/ Ethiopian Economic Policy Research Institute
Tel. 251-1- 55 74 59, 251-1 12 80 77
Fax No. 251-1 56 52 52
P.O.Box 34282, A.A Ethiopia:
e-mail: eea@telecom.net .et

EEA/EEPRI

EEA/EEPRI

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር/
የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ምርምር ተቋም

# የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ጽንሰ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ

ለድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት
ስልጠና የተዘጋጀ

ዶ/ር በፈቃዱ ደገፌ

መስከረም 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| እርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| I. መግቢያ | 1 |
| II. የኢኮኖሚ መሰረታዊ ፅንስ ሐሳብ | 3 |
| III. የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ፅንስ ሐሳቦች | 4 |
| IV. የምርት እድገት | 11 |
| V. አጠቃላይ ኢኮኖሚና የድህነት የመቀነስ ስልት | 19 |
| VI. መረሃ ግብራዊ መሣሪያዎች | 23 |
| VII. የገንዘብ መረሃ ግብር | 31 |
| IX. የውጭ ንግድና መረሃ ግብር | 42 |
| X. የውጭ ክፍያ ሚዛንና የውጭ ዕዳ | 45 |
| XI. የመስተዳድሩ ወጭና ገቢ | 48 |

# የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ፅንሰ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ

## I. መግቢያ

ዛሬ እንዳወያያችሁ የተሰጠኝ አርዕስት የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ፅንሰ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ ስልት የሚል ነው:: እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ጠቀስ አድርጌ ወደ አርዕስቱ እገባለሁ::

አንደኛው ድህነትን ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት ለኢትዮጵያ መስተዳደረም ሆነ ለሌች መስተዳደሮች ቢሆን አዲስ ግኝት አይደለም::

እግረ መንገዴን ለመግለፅ የምፈልገው በመንግስትና በመስተዳደር መካከል ልዩነት መኖሩን ነው:: ምንግስት የሚባለው ሥርዓት ህግ ደንብ ባህል ወዘተ ሲሆን መስተዳደር የሚባለው ይህን የሚያስፈፅም አካል ነው:: መስተዳደር ተለዋዋጭ ነው:: የነበረው ይሄዳል አዲስ ይመጣል:: መንግስት ግን ቋሚ ነው:: ታድያ ቋሚ ሲባል አይለወጥም ማልት አይደለም:: ህጎች፣ ደንቦች፣ የአስተዳደር ባህሎችና ወጎች ወዘተ ይለዋወጣሉ:: ግን ከተለወጠም በኋላም ያው ምንግስት ነው:: መንግስት የምንለው በእንግሊዝኛው State የሚባለው ሲሆን መስተዳደር የመንለው ደግሞ በእንግሊዝኛ Government የሚባለው ነው::

ለመንግስት መፈጠርና ብሎም መዝለቅ አንዱና ዋነኛው ምክንያት የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ላመሻሻል የሚያስችሉ ኀኔታዎችን መፍጠርና መርዳት ነው:: ይህንን ጉዳይ በሰፊው እንመለስበታለን:: ለማለት የተፈለገው ዋናው ቁምነገር ድህነትን ለማጥፋት የሚደረገውን ጥረት እንደአዲስ መታየት እንደሌለበት ነው:: ምናልባትም እንደአዲስ ይታይም ከተባላ ስልቱ ነው:: የዚህም አዲስነት አጠያያቂ ነው::

ሁለተኛው ነጥብ የአጠቃላይ ኢኪኖሚክስ ፅንሰ ሐሳብ እጅግ ሰፊና ውስብስብ ከመሆኑ የተነሳ በአጭር መግለጫ ቃሉ የቀመለትን ሙሉ ሃሳብ ለማስረዳት አዳጋች የሆነ የእውቀት ዘርፍ መሆኑን ነው:: ውስብስበ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ፅንሰ ሃሳቡ ወሳኞችንና የሚወስኗቸውን ውሳኔዎች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው:: በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ኢኮኖሚክስ ወሳኞች የሚላቸው ሦስት ቡድኖችን ነው:: እነዚህም ግለሰብ፣ ድርጅትና መስተዳደር ናቸው:: ውሳኔን በተመለከተ መሰረታዊው ጥያቄ ከላይ የተገለጹት ቡድኖች አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ እንዴት ይወስናሉ? ምን ቢሆን ምን ያደርጋሉ? የሚለው ነው:: ለምሳሌ አንድ ሰው

## ኢኮኖሚ ፅንሰ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ

ሥራ ለመስወጥ ወይም ሥራ ለመቀየር የሚያደርጉት ነገሮች ምንድንናቸው:: አንድ ሰው ይህንን ወይም ያንን ሸቀጥ የሚያስመርጠው ምንድን ነው? ድርጅት ሠራተኛ የሚቀጥረው ምን ሲሆን ነው? መንግስት ምን ሲሆን ምን ያደርጋል? እንደማለት ነው:: እንደነዚህ ላሉ ጥያቄዎች መልስ ከተገኘ ኢኮኖሚው እንዴትና ምን እንደሚሰራ፣ በቅጡ ለመምራትና ለማስተዳደር ምንና መቼ መደረግ እንዳለበት ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ይኖራል::

ከዚህ ጽሁፍ አላማ አኳያ ኢኮኖሚክስ ማለት አንድ ግለሰብ ወይም አገር ያለውን ሃብት (ገቢ) የማፍራት አቅሙን ሙሉ በሙሉ ተጠቅሞ ወይም በስራ ላይ አውሎ የኑሮ ደረጃውን በሂደት ሊያሻሽል የሚችልበትን ዘዴ ወይም ብልሃት የሚቀይስና ይህንም ተግባራዊ የሚደረግበትን ስልት የሚነድፍ የእውቀት ዘርፍ ነው::

የኢኮኖሚክስ ጽንሰሃሳብ ምንጭ ግለሰብ ነው:: ግለሰብ ማለት በተፈጥሮ ወይም በህግ የተፈጠረ ሰው ማለት ነው:: የተፈጥሮ ሰው ማለት ከእናትና ከአባት የተወለደ ሰው ነው:: ሰው የኢኮኖሚክስ ሰው የሚሆነው ዕድሜው ህግ በደነገገው መሰረት ለአቅመ አዳም ሲደርስ ነው::

በኢትዮጵያ ህግ መሰረት አንድ ሰው ለአቅመአዳም ደረሰ የሚባለው እድሜው 18ና ከዚያ በላይ ሲሆነው ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት አንድ ሰው ያለውን ሃብት የማፍራት አቅም በመጠቀም የኑሮውን ደረጃ ለማሻሻል ራሱን ችሎ ለራሱ ጠቃሚ የሆነ ውሳኔ ለመወሰን የአእምሮና የአካል ብቃት የሚኖረው ከዚህ እድሜ በላይ ሊሆን ነው የሚል ዕምነት እዚህ ውሳኔ ላይ በደረሱ የመስተዳደሩ አባላት ስለታመነበት ነው:: ዕድሜው ከ18 አመት በታች ያለው የህብረተሰብ ክፍል ጥገኛ ናቸው:: ይህ የፈጣሪ ህግ ስላልሆነ አስፈላጊና ተገቢ ነው በሚባልበት ጊዜ ሊለወጥ ይችላል::

በህግ የተፈጠረ ሰው ሲባል አንድን ህጋዊ አላማ ወይም ግብ ለመድረስ የተፈጥሮ ሰዎች የሚያቋቁሙትና በህግ ዕውቅና ያገኘ ማህበር ወይም ድርጅት ነው:: አንድ ለአካለመጠን የደረሰ ሰው ስራ የመቀጠር፣ የመቅጠር፣ የመበደር፣ የማበደር በአጠቃላይም ውል የመዋዋል፣ የመክሰስ፣ የመከሰስ መብትና ግዴታ እንዳለው ሁሉ፣ ህግ የፈጠራቸው ሰዎችም ይህ መብትና ግዴታ

ይኖራቸዋል:: ህግ የፈጠራቸው ሰዎች የሚባሉት መስተዳደር፣ የሚኒስቴር መስሪቤቶች፣ ኮሚሽኖች፣ የሙያ ማህበራት፣ የምርት፣የንግድ፣ የትራንስፖርት ድርጅቶችና የመሳሰሉት ናቸው::

## II. የኢኮኖሚክስ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳብ

### ሀ. ምኞትና አቅም

የኢኮኖሚክስ መሰረታዊ ፅንሰሃሳብ በፍላጎትና ፍላጎትን ለሟሟላት ካለ የአቅም ውስንነት ይመነጫል:: ሰዎች የተለያየ ፍላጎት አልዋቸው:: የመጀመሪያው መሰረታዊ ፍላጎቶች የሚባሉት ናቸው:: መሰረታዊ የተባሉበትም ምክንያት አንድን ሰው በህይወት ለማኖር የሚያስፈልጉ በመሆናቸው ነው:: አንድ ሰው እነዚህን ፍላጎቶች ካላሟላ በህይወት ሊኖርና፣ በህይወት በመኖርም የሚፈልገውን የተለዩ ፍላጎቶችንና መብቶችን ሊያሟላና ሊጠቀምባቸው ባለመቻሉ ነው:: እነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች ናቸው የምንላቸው ምግብ ልብስና መጠለያ ናቸው:: ማንኛውም ሰው እነዚህን ፍላጎቶች ካላሟላ በህይወት ሊኖር አይችልም:: መሰረታዊ ፍላጎቱ ከተሟላ በኋላ ያለው ፍላጎት የቅንጦት ነው::

ሌላው የሰው ባህርይ ፍላጎቱ ዳር ድንበር የሌለው መሆኑ ነው:: አንዱን ሲያሟላ ሌላ ፍላጎት ይተካል:: መሰረታዊ ፍላጎቶች ከተሟሉ በኋላ ሌሎች ፍላጎቶች በብዛት፣በአይነት፣እና ወይም በጥራት ይመነጫሉ:: አንድ ያለው ሁለት ፈላጊ ይሆናል፣ የሽሮ ወጥና የዘንጋዳ እንጀራ ያገኘ የስጋ ወጥና የጤፍ እንጀራ ይፈልጋል፣ ቶዮታ መኪና ያለው ማርቸዲስ ይፈልጋል:: ባጭሩ ሁሉ ነገር ተሟልቶልኛል፣ ምንም አልፈልግም፣ የሚል ሰው የለም:: ይህም ማለት ፍላጎትና ምኞት ዳር ድንበር የማያውቅ፣ መጨረሻ የሌለው የሰው ልጅ ባህርይ ነው::

በህግም የተፈጠሩ ሰዎች የምንላቸውም እንደዚሁ ናቸው:: አንድ ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት የህን ትርፍ ያለህ ይበቃኛል አይልም:: የሚኒስቴር መስሪያቤት ሃላፊም ቢሆን ይህን ያህል ኃይልና ሥልጣን አለኝ ይበቃኛል አይልም:: የባለስልጣናትን ስልጣንና ተግባር ለመገደብ ህግ የሚወጣውም ለዚህ ነው:: የድርጅት ባለቤቶችና የመንግስት ሹመኞች ሰዎች በመሆናቸው ድርጅታቸው ወይም

ኢኮኖሚ ዕንስ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ

መሥሪያቤታቸው አሁን ካስገኙውና ካላቸው ትርፍና ጥቅም፣ ስልጣን፣ ኃይል የበለጠ ስለሚፈልጉ።

በሌላ በኩል አንድ ሰው እነዚህን ፍላጎቶች ሊያሟላ የሚችልበት አቅም ውሱን ነው። በገቢ በኩል ሲታይ አንድ ሰው በደመወዝም ሆነ በትርፍ ወይም በተለያየ ዘዴ የሚያገኘው ገቢ ፍላጎቱን ሁሉ በአንድ ጊዜ ሊያሟላለት የሚችል አይሆንም። የገንዘብ ችግር የሌለበት ቢሆንም እንኳን ገንዘብ የማይገዛቸው ብዙ ፍላጎቶች ይኖራሉ።

ኢኮኖሚክስ መሰረታዊ ተልእኮ አንድ ሰው ወይም አንድ ገር ውሱን በሆነ አቅም ዳር ድንበር ከሌለው ፍላጎት መካከል አቅሙ የሚፈቅድለትን በመምረጥና ጊዜውንም ሆነ ሃብቱን ለተመረጡ ጉዳዮች በማዋል እንዴት አሳክቶ በደስታው ሊኖር ይችላል? ለወደፊትስ ምንና እንዴት ቢያደርግ አቅሙን አሳድጎ ገቢውን አንሮ ጊዜውን አግኝቶ ቀደምሲል ከነበረው በተሻለ ሁኔታ ፍላጎቱን አርክቶ ሊኖር ይችላል የሚለውን እንቆቅልሽ የሚፈታ የእውቀት መስክ ነው።

## ለ. የኢኮኖሚክስ ክፍሎች

ኢኮኖሚክስ በሁለት ትላልቅ ክፍሎች ይከፈላል። እነዚህም ግለሰባዊና አጠቃላይ የሚባሉት ናቸው። ግለሰባዊ ኢኮኖሚክስ የሚባለው ቀደም ሲል የተዘረዘሩት የተፈጥሮና የህግ ሰዎች ፍላጎታቸውንና አላማቸውን በብቃት ለሟሟላት የሚያደርጉትንና ማድረግ ያለባቸውን ተግባራት የሚዘረዝር፣ የሚያስረዳ፣ የሚያሳይ፣ የኢኮኖሚክስ ክፍል ነው። በእንግሊዝኛ MICROECONOMICS በመባል ይታወቃል።

አጠቃላይ ኢኮኖሚክስ በአንድ አገር ውስጥ ያለ ህዝብ ያለውን የማምረት ኃይልና ችሎታ ተጠቅሞ በተወሰነ ወቅት የሚያመርተው ምርትና የተገኘው ምርት በህብረተሰቡ አባላት መካከል እንዴት እንደሚከፋፈል፣ የተሻለ ለማምረትና ተመጣጣኝ የገቢ ወይም የምርት ክፍፍል ሊከሰት የሚችልበትን ዘዴ የሚያስረዳ፣ የሚተነትን፣ የሚያሳይ፣ የኢኮኖሚክስ ክፍል ነው። በእንግሊዝኛ MACROECONOMICS በመባል ይታወቃል።

ኢኮኖሚክስን ለሁለት ክፍለን በምናይበት ሁኔታ በመካከላቸው ያለው ልዩነት የአላማ ሳይሆን ትኩረት ከተደረገበት የጉዳዩ ባለቤት አንጻር ብቻ ነው:: በሁለቱም ክፍሎች ሚደረገው ጥናት፣ ምርምር ትንተና አላማቸው አንድ በመሆኑ:::

ከአላማ አንፃር ማለትም ለምን የኢኮኖሚክስ ጥናትና ምርምር ይካሄዳል ከሚል አኳያ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ከዚህ አንጻር የኢኮኖሚክስ ጥናት፣ ምርምርና ትንተና አላማ ወይም ግብ በሁለት ይከፈላል:: አንደኛው ገላጭ ኢኮኖሚክስ ብለን ልንሰይመው እንችላለን:: ይህም በእንግሊዘናው Posetive Economics የሚባለው ነው:: በዚህ ክፍል የሚካተተው ኢኮኖሚክስ ጥናት፣ ምርምርና ትንተና አላማ ኢኮኖሚው እንዴት እንደሚሰራ፣ ምን በደረግ ወይም ቢሆን ምን ውጤት ሊመጣ እንደሚችል፣ ወዘተ የሚያስረዳ፣ የሚያሳውቅ፣ የሚያስገነዝብ ነው:: ገላጭ ኢኮኖሚክስ አንድ ግብ ለመድረስ ምን ቢደረግ ይሻላል፣ ኢኮኖሚው አሁን ባላበት ሁኔታ ቢመራ ይሻላል ወይስ ይለወጥ፣ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ምን ማድረግ ይሻላል፣ ድህነትን ለመቀነስ ምን ይደረግና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አንስቶ እንዲህ ቢሆን ይሻላል የሚል ብይናዊ መልስ አይሰጥም:: ያለውንና የሆነውን ብቻ የሚያስረዳ ነው:::

ከአላማ አንጻር ሁለተኛው ብይናዊ ብለን የምንጠራው ነው:: ይህም በእንግሊዝኛው Normative Economics የሚባለው ነው:: ብይናዊ ኢኮኖሚክስ ያለውን ሁኔታ ተንትኖ የተሻለ ሁኔታ ለመፍጠር ምን መደረግ እንዳለበት፣ አንደ ግብ ነድፎ ወደዚያ የሚያደርሱ መርሃግብራዊ አማራጮችን መርምሮ የተሻለውን መምረጥና ተገቢውን ስልት መቀየስና፣ የመሳሰሉትን ሥራዎች የሚያካሂድ ኢኮኖሚክስ ክፍል ነው::


## III. የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ጽንሰ ሐሳቦች

ከዚህ በሚቀጥሉት ገጾች የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ጽንሰ ሀሳብ ይቀርባሉ::

### ሀ. የገቢ ዑደት

ገቢና ወጪ በአገርና በህብረተሰብ ደረጃ አንድ ናቸው:: የአንዱ ሰው ወጪ የሌላው ሰው ገቢ በመሆኑ:: በአገር ደረጃ ይህ እውነትነት አለው:: የአንዱ ገቢ እንዴት ለሌላው ወጪ እንደሆነና ይህም የሚፈጥረውን ዑደት፡ በሚቀጥለው ገጽ ያለውን ስዕል በመታገዝ ለመረዳት መረዳት ይቻላል::

1) ቤተሰብ ያለው ጉልበትና ዕውቀት ነው:: ይህንን ለድርጅቶች ያከራያል (መስመር 1)::
2) ድርጅቶች ከቤተሰብ ለተከራዩት ጉልበትና ዕውቀት በገበያው ዋጋ መሰረት ደመወዝ ይከፍሉ:: ይህ ለድርጅቶች ወጪ ለቤተሰብ ደግሞ ገቢ ይሆናል (መስመር 2)::
3) ድርጅቶች ከቤተሰብ የተከራዩትን ጉልበትና እውቀት በመጠቀም ምርት ያመርታሉ:: ምርቱን ለቤተሰብ ይሸጣሉ (መስመር 3)::
4) ቤተሰብ ምርቱን በደመወዝ ባገኘው ማነዘብ ይገዛል (መስመር 4):: ይህ ለቤተሰብ ወጪ ሲሆን ለድርጅቶች ገቢ ነው::




ይህ ዑደት ሌሎች ክፍሎችም ቢጨመሩበት አቀራረቡን ውስብስብ የደርገው እንደሁ እንጂ መሰረታዊ ነጥቡን አይለውጥም:: ለምሳሌ መስተዳደሩና ባንኮች በዚህ ዐደት ውስጥ ቢጨመሩ ፋይዳውን አይለውጠውም:: መስተዳደሩ በግብርና በቀረጥ ከግለሰቦችና ከድርጅቶች ገንዘብ ይሰበስባል:: በፋንተውም በዚህ ገንዘብ ከቤተሰብ ዕውቀትና ጉልበትን፡ ከድርጅቶች ምርትን

ይሸምትበታል። ባንኮች የቤተሰቦችንና የድርጅቶችን ቁጠባ በመሰብሰብ። ለቤተሰቦችና ለድረጅቶች መልሰው ያበድራሉ።

ከዚህ ዑደት ወጣ የሚል ነገር ሊያጋጥም የሚችለው የውጪና የገቢ ንግድ ሲታከልበት ነው። የወጪ ንግድ ያገርን ምርት ወደ ውጭ ስለሚሸጥ ገቢን ያሳድጋል። ስራ እድልም ይፈጥራል። በገቢ ንግድ የሌላ አገር ምርት ስለምንገዛ ገቢአችንን ይቀንሳል። ገቢችን ከአገር ውጭ ይፈሳል ማለት ነው። ለዚህ ጥሩ ተምሳሌት የአባይ ወንዝ ነው።

## ለ. የአመራረት ሂደትና የኢኮኖሚ ሞተር

የአመራረት ሂደት የምንለው አምራቾች ድርጅት አደራጅተው ምርት የማምረታቸውን ሂደት ነው። ይህን በሚቀጥለው ገጽ ያለውን ምስል በመተቀም መገንዘብ ይቻላል።
ሰው የማምረቻ መሣሪያዎችን በመጠቀም ከተፈጥሮ ሊገኝ የሚችለውንና ለሰው ጠቃሚ የሆነውን ምርት ያመርታል። በእውቀቱና በጉልበቱ የምርት መሣሪያዎችንም ያመርታል።

### ምርትን ለማሳደግ ሰው፡-

ሀ) ጉልበቱን ማዳበር አለበት። በቂ ጉልበት የሳለው ደካማ ሰው ምርቱ ትንሽ ይሆናል። ጉልበቱ ኃይለኛ ከሆነ ግን ምርቱ ከፍተኛ ይሆናል። ስለዚህም በቂ ጉልበት እንዲያገኝ በቂ ምግብና ጤንነቱም መጠበቅ ይኖርበታል። የበቂ ምግብ፣ ንጹህ ውሃ፣ ህክምና ወዘተ አቅርቦት እዚህ ላይ ወሳኝነት አለው።

ለ) ዕውቀት ያስፈልገዋል። ያለ እውቀት ምንም ለማምረት አይቻልም። የአገራችን ገበሬ ሲወርድ ሲወራረድ የነበረ ዕውቀት ተጠቅሞ ምርት ያመርታል። እውቀቱ ግን ኋላ ቀር በመሆኑ የሚመርታው ትንሽ ነው። ችግሩ ያለው ከሚያፈሰው ጉልበት ማነስ ወይም ከተፈጥሮ ልግመት ሳይሆን የሚጠቀመው እውቀትና የማምረቻ መሣሪያ ኋላ ቀርነት ነው። ይህም ምርታማነቱን በእጅጉ ይገታዋል። ስለዚህም የግብርና ዕውቀቱን፣ ማምረቻ መሣሪያውንና ግብአቶችን ዘመናዊ ማድረግ ያስፈልገዋል። ይህም የሚገኘው በትምህርትና በስልጠና እንዲሁም በአገር ውስጥ በሚደረግ ስርፀት የሚገነባ የተሻሻለ


የምርት መሳሪያ ነው። የምርት ሞተር ምንድነው? አምራቾችን የማያበረታታና የሚያንቀሳቅሰው ምንድነው? የነዚህና የነዚህ መሰል ጥያቄዎች መልስ ስለዕድገት የሚያጠኑትን ኢኮኖሚስቶች ቀልብ ይስባል። መልሱን ካወቅን እድገታችንን ብሎም ልማታችንን የሚቀይዱትን ደንቃራዎች አውቀን ችግራችንን ልንወጣ እንችላለን። እስከ 1928/29 ድረስ የኢኮኖሚስቶች የምርት ሞተር ምንድነው ለሚለው ጥያቄ አንድ አቋም ይዘው አምራች ነው ይሉ ነበር። ምክንያቱም አምራች ካመረተ ገበር ይከተላል የሚል ከፍተኛ እምነት ነበራቸው። ይህም የሴይ ህግ በመባል ይታወቃል። ምን ይመረት፣ ምን ያህል ይመረትና ለማን ይመረታል ሲባሉ ይህን ገበያ ውስጥ ያለው የአቅርቦትና የፍላጎት ኃይል ይወስናል ነው ይሉ የነበረው። ይህም የገበያ ህግ በመባል ይታወቃል። በመሆኑም መስተዳደሩ በዚህ ጉዳይ ጣልቃ መግባት የለበትም ይሉ ነበር።

በ1928/29 ኬይንስ የሚባል እንግሊዛዊ ኢኮኖሚስት የሲይን ሕግ በአናቱ አቆመውና ምን ያህል ምርት መመረት እንዳለበት የሚወስነው አምራቹ ሳይሆን ገበርው ነው የሚል ህግ ፈለሰፈ። ገበሬው ምን ያህል ማምረት እንዳለበት የሚወስነው ገበያ አለ? የማመርተው ይሸጥልኛል? በማለት ነው። አንድ ድርጅት አምርቶ ገበያ ካላገኘ አያመርትም። ስለዚህ መስተዳደሩ የሸማቾችን የመግዛት ኃይል ማጠናከር አለበት። ምርት ተመርቶ ገበር ከጠፋ መስተዳድሩ እራሱ ሸምቶ የሚያደርገውን ማድርግ ይኖርበታል። መስተዳደሩ የሚያደርገው ካጣ ሥራ አጦችን ሰብስቦ ግማሹ ጠዋት ቦይ ይቆፍር። ግማሹ ከሠአት ጠዋት የተቆፈረውን ቦይ ይድፈን። ከዚህም በሚያገኙት ገቢ ምርት ይሸምታሉ። አምራቹ ገበያ ካገኘ ሰው ይቀጥራል። ስራ አጥነትም ይጠፋል ሲል ተሟገተ። ረታም። ከዚያ በኋላ መስተዳደሮች በኢኮኖሚው ውስጥ ጉልህ ሚና መጫወት ጀመሩ።

ከዚያ ጊዜ በኋላ ሠራተኛው በዝቶ፣ ስራ አጥነት ከስምኖ ሰው ሁሉ ገቢ አግኝቶ የመግዛት ኃይሉን አጠናክሮ ገበያ ሄዶ ምርት ሊሸምት የሚችልበትን ዘዴ የመቀየስና ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነትን ተሸከመ።

በመሆኑም የመስተዳደሩ ኢኮኖሚያዊ መርሃግብር ምርት እንዴት ይድጋል? አምራቹ እንዴት ይበረታታል? የሥራ ዕድል እንዴት ይስፋፋል? ገበያ ዋጋ እንዴት ይሰክናል? ገቢ በፍትሃዊነት እንዴት ይከፋፈላል?ና በመሳይ ጥያቄዎች ዙርያ ለማጠንጠን ተገደደ:: ይህ ሃሳብ በተለይም በአሁኑ ጊዜ በደሃ አገሮች ተቀባይነቱ የጠነከረ ቢሆንም ተፋላሚዎች አልጠፉም:: በተለይም የአለም ባንክና የአለም ገንዘብ ድርጅት የአቶ ሴይን ህግ በማንገብ ምርትን ገበያው ይወስን:: ምርቱ በገበያ ተቀባይነት ያለው ብቻ ያምርት:: አለም የሁሉም አገር አምራቾች ትሁን:: መስተደሰደሩ በገበያ ውስጥ ጣልቃ ሳይገባ በየትም አገር የተመረተ ምርት በማንኛውም አገር ገበያ ይቅረብ በማለት ከመከራከርም አልፈው ደሃ አገሮች ተግባራዊ እንዲደርጉ ያስገድዷቸዋል::

## የምርት ሂደት ማገናዘቢያ ሥዕል



## IV. የምርት እድገት

ድህነትን ለማጥፋት እያንዳንዱ ግለሰብ ከድህነት ለመውጣት የራሱን ጥረት ማድረግ አለበት። የመንግስት የመጀመሪያውና መሰረታዊ ሃላፊነት ግለቦች ሊከብሩና ከድህነት ሊወጡ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።እነዚህ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ፣ እንዴትስ ሊፈጠሩ እንደሚችሉ በዝርዝር ከማየታችን በፊት ምርት እድገት እንዴት እንደሚለካ መረዳት ያስፈልጋል።

### ሀ. ምርትን መለካት

እንደሚታወቀው በሃገራችን በብዙ መቶ ሚቆጠሩ የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶች በተወሰነ ጊዜ ይመረታሉ። የእነዚህ የተለያዩ ምርቶች ድምር በዚያን ዘመን የተመረተ ምርት ይባላል። በሚቀጥለው የምርት ዘመን በአለፈው የምርት ዘመን የተመረቱትንና አዳዲስም ጨምሮ ይመረታል። ምርት አደገ ወይም ቀነሰ ስንል በዘንድሮው የምርት ዘመን የተመረተውን ከአለፈው የምርት ዘመን ከተገኘው ምርት ጋር በማነጻጸር የሚደረስበት ውጤት ነው። ይህንን ንጽጽር ለማድረግ አንዱ መንገድ ገበሬ ወይም ፋብሪካ ዘንድሮ ያመረተውን አምና ካመረተው ጋር ማነጻጸር ያስፈልጋል።

ይህን ንጽጽር ለማድረግ አንዱ መንገድ እያንዳንዱ ገበሬ ወይም ፋብሪካ ዘንድሮ ያመረተውን በቆሎ ጤፍና የመሳሰሉትን ምርቶች በማየት ሊደረስበት ይችላል። ሆኖም ግን ይህ አዳጋችና አሰቸጋሪ ነው። አንዱ ችግር እያንዳንዱን ገበሬ ወይም የኢንዱስትሪ ባለቤት የዘንድሮው ምርት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር ምርቱ አደገ ወይስ ቀነሰ ወይስ ተመጣጣኝ ነበር ብሎ በመጠየቅና ትክክኛውን መልስ እነዚህ ሰዎች ከሰጡ ምርት ማደግ አለማደጉ ሊታወቅ ይችላል። ሆኖም ግን እንዲህ ዓይነት ስሌት የሚሠራው ለያንዳንዱ ምርት እንጂ በአጠቃላይ በአገሪቱ የተመረተውን ምርት አይሆንም። የተመረተው በቆሎ አደገ ለማለት በአገሪቱ ዘንድሮ የተመረተውን በቆሎ በሙሉ ደምረን አምና ከተመረተው በቆሎ ጋር በማነፃፀር የበቆሎ ምርት ማደግ ወይም አለማደግ ልናውቅ እንችላለን። ለሌሎች የግብርና ምርቶች እንዲሁ እያንዳንዱን ለይተን ለብቻው ልናጣጽር እንችላለን። ነገርግን በዚህ ዘዴ የሚገኘው ስሌት በአጠቃላይ የግብርና ምርት አደገ ወይም

አላደገም ለማለት አያስችልም። ምክንያቱም በቆሎውን ዘንጋዳውን፣ ስንዴውን ጤፉን ወዘተ አንድነት ለመደመር ስለማይቻል በመሆኑ።

እንዲሁም በኢንዱስትሪዎቻችን የሚመረተው ጫማ፣ ሳሙና፣ ቆርቆሮ ፓስታ ማደግ አለማደጉን የያንዳንዱን የዘንድሮ ምርት ከአምናው ጋር በተናጥል በማነፃፀር ለማወቅ እንችላለን። ሆኖም ግን ይህ አሰራር የኢንዱስትሪው ዘርፍ ምርት በአጠቃላይ ማደግ አለማደጉን ለማወቅ አያስችለንም። ምክንያቱም ጫማና ሳሙና፣ ቆርቆሮና ፓስታን አንድነት ለመደመር ስለማንችል።  በዚህም ሊቆጠሩ የማይችሉ ብዛት ያላቸው የአገልግሎት ዘርፍ ምርቶች አሉ። ለምሳሌ ባንክና ኢንሹራንስ፣ ንግድ፣ ትምህርት፣ ጤና፣ የአገር መከላከያ ደህንነትና ከመሳሰሉት ዘርፎች በአይን የሚታይ በእጅ የማይዳሰስና በመሆኑም የማይቆጠር ነገርግን በኢኮኖሚው ውስጥ እጅግ ተፈላጊ ማና የሚጫወቱ ምርቶች አሉ።

የአገር ኢኮኖሚ ሲባል እነዚህን ሁሉ ማለትም ግብርናውን፣ ኢንዱስትሪውን የአገልግሎቱን ዘርፍ ያካተተ በመሆኑ ስለእድገት በሚወሳበት ጊዜ እነዚህን ሁሉ አንድነት የሚያዳምር ዘዴ ካልተፈጠረ በአጠቃላይ ለመተመን አይቻልም። ለምን ቢባል በቆሎ፣ ዘንጋዳ፣ ጫማ፣ቢራ፣ ንግድ የመንግስት አስተዳደር ወዘተ ምርቶች የተለያዩ ስለሆኑ አንድነት ደምሮ የአገር ውስጥ ምርት አደገ ወይም ቀነሰ ብሎ ስለማይቻል ነው።

ከዚህ ችግር ለመውጣት ኢኮኖሚስቶች የነደፉት ዘዴ በአገሪቱ የተመረቱትን ምርቶች በሙሉ በአንድ መለኪያ መለካት ነው። ይህም መለኪያ ገንዘብ ነው። በመሆኑም በአገራችን የሚመረቱ ምርቶች በሙሉ  በብር ተተምነው ዘንድሮ ይህን ያህል ተመረተ ይባላል። አምና ወይም ከዚያም ቀደም ሲል በነበሩት አመታት የተመረተውን ምርት በማነፃፀር እድገት መኖር አለመኖሩ ይታያል።

## ለ. የአገር ውስጥ ምርትን የመተመኛ ዋጋ

የተመረተው ያገር ውስጥ ምርት እሴት ወደገንዘብ ተለውጦ ሁሉም በአንድ መለኪያ የመለካቱን አስፈላጊነት ከተረዳን ዘንዳ የሚከተለው ጥያቄ በየትኛው ዋጋ ይተመን የሚለው ነው:: ለዚህ መልስ ከአላማው ይመነጫል:: የሚፈለገው የምርት ትመና ለምን አገልግሎት ሊውል ታስቦ ነው የሚለው መሰረታዊ መነሻ ይሆናል:: አምራቹ ምርቱን ለማምረት ምን ያህል እንዳወጣ ለማወቅ ከተፈለገ ምርቱ በተመረተበት ዋጋ ይተመናል:: ይህም በእንግሊዝኛ Output at Factor Cost የሚባለው ነው:: በአንፃሩ የመጨረሻው ተጠቃሚ ከከፈለበት አንጻር ሲታይ ምርቱ በገበያ ዋጋ ይተመናል:: ይህም በእንግሊዝኛው Output at Market Price የሚባለው ነው::

## ሐ. ምርት በየትኛው ዘመን ዋጋ ይተመን?

ከዋጋ ጋር የተያያዘው ሌላው ጥያቄ ምርት በየትኛው ዘመን ዋጋ ይተመን የሚለው ነው:: ያለው አማራጭ ሁለት ነው:: አንዱ በዘመኑ ዋጋ ሲሆን ሌላኛው በአንድ በተመረጠ አመት በነበረው ዋጋ መተመን ነው::

የዚህን አስፈላጊነት ለመረዳት የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት:: አምናም ዘንድሮም እኩል 10 ኩንታል ጤፍ አመረትን እንበል:: አምና የጤፍ ዋጋ በኩንታል 300 ብር ነበር እንበል:: ዘንድሮ ዋጋው ወርዶ 200 ብር ሆነ:: በዘመኑ የገበያ ዋጋ ሲተመን የዘንድሮው የጤፍ ምርት 2000 ብር ሲሆን ያምናው 3000 ብር ነበር:: ታድያ ዘንድሮ ከአምናው ያነሰ አመረትን ማለት ነው? ሌላ ምሳሌ:: አምና 100 ጫማ ተመርቶ ባንድ መቶ ብር ተሸጠ:: ያመረትነው ጫማ 1000 ብር ነበር ማለተ ነው:: ዘንድሮ 50 ጫማ አምርተን በ 200 ብር ተሸጠ:: ምርቱ እኩል ነው ማለት ነው? የተመረተው በዘመኑ በነበረው ዋጋ ሲታይ ይመስላል:: ይህንን ያደረገው የዋጋ መለያየት ነው:: የዘንድሮውን ጤፍና ጫማ ምርት በአምናው ዋጋ ወይም በዘንድሮው ዋጋ ብንለካቸው ግን ትክክለኛውን ሁኔታ ለመረዳት አያዳግተንም:: ስለዚህም ነው ትክክለኛውን የምርት እድገት ለማግኘት የተለያዩ አመት ምርቶችን አንድ አመት በነበረ ዋጋ የምናሰላው::

## መ. የአገር ውስጥ ሽያጭና የአገር ውስጥ ምርት

የአገር ውስጥ ምርት ከአምራቹ ወደ ተጠቃሚው እስኪደርስ ድረስ የተለያዩ ሰዎች ገዝተው እነሱም በበኩላቸው እሴት ጨምረውበት ከገዙበት ዋጋ ከፍ አድርገው ይሸጣሉ፡፡ በአገር ውስጥ የሚደረገው የምርት ልውውጥ ድምር ሽያጭ ይባላል፡፡ የዚህ እሴት አገር ውስጥ ከተመረተው በጣም የሚበልጥ ነው፡፡ ምክንያቱም በአገራችን የተደረገው የሽያጭ ድምር ምርት ከአንድ ሰው ወደሌላው በሚዞርበት ጊዜ በድግግሞሽ ተደምሮ የተደረሰበት በመሆኑ ነው፡፡ ይህንን በምሳሌ ለማስረዳት አንድ ኩንታል ስንዴ እንውሰድ፡፡ አንድ ኩንታል ስንዴ ገበሬው በብር 200 ሙቶ ለወፍጮ ቤት ይሸጣል፡፡ ወፍጮ ቤት ይህንን ስንዴ ፈጭቶ በብር 250 ለዳቦ ጋጋሪ ይሸጣል፡፡ ዳቦ ጋጋሪው የገዛውን ዱቄት ወደ ዳቦ ለውጦ ዳቦውን በብር 300 ይሸጣል፡፡ ስንዴው ከገበሬው ጀምሮ ዳቦ በላተኛው ጋ እስኪደርስ ድረስ የተካሄደው የሽያጭ ድምር ብር 750 ነው፡፡ ይህ ብር 750 የአገር ውስጥ ምርትን አይለካም፡፡ ምክንያቱም አንድ ምርት ከአንዱ ወደ ሌላው ተላልፎ የተከፈለውን ሁሉ ስለሚጨምር ነው፡፡ የአንድ ምርት ዋጋ በድግግሞሽ ይደመራል ማለት ነው፡፡ የስንዴውን ምርት ለማስላት ሁለት ዘዴዎች አሉ፡፡ እነሱም በያንዳንዱ ደረጃ የተጨመረውን እሴት ብቻ በመደመር የሚገኝ ሲሆን ሁለተኛው የመጨረሻው ተጠቃሚ የሚከፍለው ነው፡፡ እነዚህን ለመረዳት የሚቀጥለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡፡

ሰንጠረዝ 1

| የሽያጭ ምርት አተማመን | | |
|---|---|---|
| | የተሸጠበት (ብር) | የተጨመረ እሴት (ብር) |
| 1. ገበሬ | 200 | 200 |
| 2. ወፍጮ ቤት | 250 | 50 |
| 3. ዳቦ ጋጋሪ | 300 | 50 |
| 4. መጨረሻ ተጠቃሚ የከፈለው | 300 | |
| 5. ጠቅላላ ሽያጭ | 750 | |
| 6. የምርት እሴት | | 300 |

ሰንጠረዡ እንደሚያስረዳው አንዱን ኩንታል ስንዴ ከገበሬው የመጨረሻ ተጠቃሚ እስኪደርስ ድረስ የተካሄደበት የሽያጭ እሴት ብር 750 ነው፡፡ እዚህ ላይ የስንዴው ዋጋ ሦስት ጊዜ ተደምሯል፡፡ ገበሬው የሸጠበት ወፍጮ ቤት የሸጠበትና ዳቦ ጋጋሪው የሸጠበት፡፡

እንደዚህ ዓይነት ስሌት በየደረጃው የተጨመረበትን እሴት ጨምሮ የተደረሰበት የንግድ ውጤት ነው። የምርት እሴት ሲሰላ ድግግሞሹን ማስቀረት የግድ ነው። በመሆኑም ምርቱ የሚሰላው በሁለት ዘዴ ነው። ይህም፣

1) በየደረጃው የተጨመረ እሴትን ብቻ በመደመር ይህም በሰንጠረዥ /ሁለተኛ አምድ የሚታየው ነው። በዚህ ተጨማሪ እሴት ፈጠራ መሠረት ገበሬው የፈጠረው እሴት ብር 200 ነው። የወፍጮ ቤቱ የሸጠው በብር 250 ሲሆን ብር 200 የገበሬው የፈጠረው እሴት ሆኖ ወፍጮ ቤቶች ስንዴውን ወደዱቄት ለመለወጥ የጨመረው እሴት ብር 50 ነው። የዳቦ ጋጋሪው ሽያጭ 300 ሆኖ ይህም የገበሬውን ብር 200፣ የባለወፍጮውን ብር 50 እንዲሁም ዱቄቱን ወደ ዳቦ በመለወጥ የጨመረውን አዲስ ወይም ተጨማሪ እሴት ብር 50ን ያካተተ ነው።

 በዚህ መሠረት አንዱ ስንዴው ከስንዴነት ወደ ዳቦ እስኪለወጥ ያለው የምርት እሴት ብር 300 ይሆናል። ሁለተኛው የምርት አሰላለ ዘዴ የመጨረሻው ተጠቃሚው የከፈለው ዋጋ ይሆናል። እዚህ ላይ የመጨረሻው ተጠቃሚ ዳቦን የሚበላው ሲሆን እሱም የከፈለው የዳቦ ጋጋሪው የሸጠበት በመሆኑ ይህም ብር 300 ይሆናል።

 በነዚህ ሁለት ዘዴዎች የሚደረስበት የምርት እሴት እኩል ናቸው። መሆንም አለባቸው። የአገር ምርትም የሚተመነው ከነዚህ ከሁለት አንዱ ዘዴ ነው።

## ሠ. የኢትዮጵያ የሐገር ውስጥ ምርት

በአገራችን የተመረተው ምርት እያንዳንዱን የመጨረሻው ተጠቃሚ በከፈለው ዋጋ ወይም በደረጃው በተጨመረው እሴት አዳምረን ልንደርስበት እንችላለን። ይህም ጠቅላላ የሐገር ውስጥ

ኢኮኖሚ ፅንሰ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ

ምርት የሚባለው ነው:: በእንግሊዝኛ Gross Domestic Product የሚባለው ነው:: ስሙ እንደሚያመለክተው ጠቅላላ የሐገር ውስጥ ምርት በተወሰነ ጊዜ የተመረተ አጠቃላይ ምርት ነው:: ሆኖም ግን በአገራችን የተመረተው ሁሉ የኛ ገቢ ወይም ንብረት ላይሆን ይችላል:: ምክንያቱም የውጭ አገር ሰዎች በአገራችን ተቀጥረው ሆነ ወይም መዋዕለ ንዋያቸውን አፍስሰው ይሠራሉ:: እነዚህ ሰዎች ካፈሩት ምርት ውስጥ የተወሰነውን ያህል ወደ አገራቸው ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ወደፈለጉት አገር ይልካሉ:: በአንጻሩም ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ካገኙት ገቢ ለዘመዶቻቸው የሚልኩ አሉ:: ከዚህም ሌላ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሐብታቸውን አውጭ ሐገር ቢያስቀምጡና ወይም ቢሠሩበትና ከዚያ የሚገኘው ገቢ ወደ አገር ውስጥ ሊያመጡ ይችላሉ::

ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት የሚባለው በአንድ ዓመት በአገራችን ከተመረተው ምርት ከውጭ አገር የተገኘ የተጣራ የሥራና የንብረት ገቢ ጋር ተደምሮ የሚገኘው ነው:: ይህም በእንግሊዝኛው Gross National Product የሚባለው ነው::

በኢትዮጵያ የተመረተውን ጠቅላላ ምርት የሚቀጥሉትን ሰንጠረዦች በመንተራስ በአጭሩ እናሳያለን::

በ1991 ዓ/ምህረት በዚያን ዓመት በነበረው የገበያ ዋጋ ብር 48.7 ቢሊዮን የሚያወጣ ምርት አምርተናል:: ይህ ምርት በ1973 ዋጋ ሲተመን ብር 15.5 ቢሊዮን ነው:: በሁለቱ መሃል ያለው ልዩነት ከ 1973 እስከ 1991 ባሉት ጊዜአት የነበረውን የገበያ ዋጋ ልዩነት ያንጸባርቃል:: ይህም ማለት በሁለቱ አመትት መካከል የገበያ ዋጋ በ 215 በመቶ አድጓል ማለት ነው::

ይህ በገበያ ዋጋ ሲሆን ይህ ምርት በ 1973 በተሰራበት ዋጋ ቢሰላ ኖሮ እሴቱ ብር 15.5 ቢሊዮን ይሆናል:: ይህ ምርት ምንድነው? ከየት የመጣ ነው? የት የተመረተ ነው? እነዚህን ጥያቄዎች ሠንጠረዥ ሁለት ይመልሣል:: ከግብርና የተገኘው 6.9 ቢሊዮን ብር ሲሆን ይህም ከጠቅላላው ምርት 45 በመቶ ይሆናል:: ከኢንዱስትሪ የተገኘው ብር 1.8 ቢሊዮን ሲሆን ይህም በመቶ 12 ብቻ ነው:: ካገልግሎት የተገኘው ብር 2.3 ቢሊዮን ከማከፋፈልና ብር 4.5 ቢሊዮን ከልዩ ልዩ ገልግሎት ነው:: የአገልግለት ድርሻ ከጠቅላላ ምርት 44 ከመቶ ነው::

ሰንጠረዥ 2
የሐገር ውስጥ ምርት
(በሚሊዮን ብር)

| | 1990 | 1991 |
|---|---|---|
| ጠቅላላ የሐገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ | 44840.3 | 48687.6 |
| ጠቅላላ የሐገር ውስጥ ምርት በተሠራበት የ1973 ዋጋ | 14542.6 | 15460.3 |
| ጠቅላላ ምርት በምንጭ በ1973 ዋጋ | 14542.6 | 15460.9 |
| ግብርና | 6648.9 | 6904.2 |
| ኢንዱስትሪ | 1630.9 | 1815.8 |
| ማዕድንና ድንጋይ ማውጣት | 68.9 | 75.4 |
| ፋብሪካዎች | 621.8 | 744.9 |
| አደ ጥበብና ትናንሽ ፋብሪካዎች | 305.0 | 318.9 |
| ህንጻና መንገድ ሥራ | 412.1 | 442.6 |
| መብራት፣ ኤሌክትሪክ ኃይልና ውሐ | 223.1 | 233.9 |
| ከማከፋፈያ ሥራ | 2177.9 | 2253.9 |
| ንግድ ሆቴልና ሬስቶራንት | 1263.3 | 1343.9 |
| መጓጓዣና መገናኛ | 914.6 | 910.0 |
| ከልዩ ልዩ አገልግሎቶች | 4085.0 | 4487.0 |
| ባንክና ኢንሹራንስ | 1002.2 | 1044.3 |
| አስተዳደረና መከላከያ | 1848.3 | 2138.5 |
| ትምህርት አገልግሎት | 327.0 | 348.6 |
| ህክምናና ጤና አገልግሎት | 175.9 | 187.6 |
| ከቤት ውስጥ አገልግሎትና ሌሎች | 731.5 | 768.1 |

ምንጭ ኢልትሚ

አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ የአገልግሎቱ ድርሻ እጅግ የናረ ነው። መሆን የነበረበት የእቃ አምራች ድርሻ ከፍ ማለት ነበረበት። የሚሸጥ ነገር ሳይኖር ንግድ ከፍ ያለ የአስተዳደር ወጪ, አለ ማለት ነው።

## ይህን ምርት ምን አደረግንበት?

ከተመረተው አንፃር ሲታይ ያመረትነው ምርት ሀ) ለአገር ውስጥ ለግል ፍጆታ የሚውል ነው። ይህም እንደምግብ፣ልብስ፣ ጫማ ወዘተ ያለ ማለት ነው። ለ) ሁለተኛው ለመንግስት አገልግሎት የሚውል ነው። ይህም የጽህፈት፣ የመከላከያ መሣሪያ ወዘተ ማለተ ነው። ሐ) ሶስተኛው

ለምርትና ለግንባታ የሚያገለግሉ ምርቶች ናቸው። ይህም ሲሚንቶ፣ ብረታብረት ወዘተ ማለት ነው። መ) አራተኛው ወደ ውጭ ለመሸጥ ያመረትናቸው ናቸው። እነዚህም ቡና፣ቆዳና ሌጦ ወዘተ ማለት ነው። እነዚህ አራቱ ሲደመሩ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ይሆናሉ። በአንፃሩ ከውጭ ያስገባነው ምርት አለ።

በአገር ውስጥ በአመቱ ለፍጆታ፣ ለምርት ኃይል ማዳበሪያ፣ ለመስተዳደር ለግል ፍጆታ፣ ወደ ውጭ የተጠቀምንበት ምርት የነዚህ ሁለቱ ድምር ይሆናል ማለት ነው። ይህ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ተካቷል።

ሠንጠረዥ 3
ጠቅላላ ብሔራዊ ወጪ
በዘመኑ የገበያ ዋጋ
(ሚሊዮን ብር)

| | 1990<br>1997/98 | 1991<br>1998/99 |
|---|---|---|
| ጠቅላላ የሐገር ውስጥ ወጪ | 48565.7 | 56772.6 |
| የፍጆታ ወጪ | 40875.1 | 48966.7 |
| መስተዳደር | 6251.4 | 9127.0 |
| ግል | 34623.7 | 39839.6 |
| የምርት አቅም ግንባታ | 7690.6 | 7805.9 |
| ጠቅላላ ብሔራዊ ገቢ | 45034.9 | 48464.3 |
| የወጪና ገቢ ሚዛን | (3530.8) | (8308.3) |
| የወጪ ንግድ | 7136.6 | 6863.4 |
| የገቢ ንግድ | 10667.4 | 15171.7 |
| | | |
| የአገር ውስጥ ቁጠባ | | |
| ከውጭ የተሰጠ የሥራና የንብረት ገቢ | 4159.8 | (502.4) |
| ከውጭ የተሰጠ ገቢ | (238.7) | (211.8) |
| ብሔራዊ ቁጠባ | 3726.4 | 3690.4 |
| | 7647.4 | 2976.2 |

ምንጭ፡ ብሄራዊ ባንክ።

ከአገር ውስጥ ወጪ ሰንጠረዥ የሚያስረዳን አብይ ጉዳይ ከገቢያችን ወጪአችን መብለጡን ነው። ገቢያችን ብር 48.5 ቢሊየን ሲሆን ወጪአችን ብር 56.8 ቢሊየን ነው። ብር 8 ቢሊየን ከውጭ በልመናና በብድር መሆኑ ነው። ይህን ዝቅ ብለን እናየዋለን።

## V. አጠቃላይ ኢኮኖሚና ድህነት የመቀነስ ስልት

### ሀ. ድህነት ምንድነው?

ድህነት በአይነት የተለያየ ነው። የፖለቲካ ድህነት፣ የመብት ድህነት፣ የአስተሳሰብ ድህነት፣ የኢኮኖሚ ድህነት ወዘተ ናቸው። እነዚህንና ሌሎችን የድህነት አይነቶች ነጣጥለን እንያቸው እንጂ የተዛመዱ፣ አንዱ ሌላውን የሚፈጥርና የሚከተል የሚያባብስ መሆኑን መገንዘብ ያሻናል።

በዚህ ገለጻ ትኩረት ሰጥተን የምንመለከተው የኢኮኖሚ ድህነትን ብቻ ነው።

### ለ. የኢኮኖሚ ድህነት መገለጫዎች

የኢኮኖሚ ድህነት ስንል አንድ ሰው ለኑሮ መሰረታዊ ፍላጎቶች ተብለው የተፈረጁትን እደ ምግብ፣ መጠለያ፣ እና ልብስ በበቂ አለማግኘት ማለት ነው። የኢኮኖሚ ድህነት ከምርት በበቂ አለመመረትና ወይም ከስራ አጥነት ይመነጫል።

### ሐ. የህዝብ ብዛትና ልማት

ድህነትን ለመቀነስና ብሎም ለማጥፋት መሰረታዊ መፍትሄ የኢኮኖሚ እድገት መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጧል። ዕድገቱ ምን ያክል ቢሆን ነው ይህ ሁኔታ የሚሳካው የሚል ጥያቄ ተገቢ ነው። ለዚህ የሚሰጠው አጭር መልስ የኢኮኖሚው ዕድገት ከህዝብ እድገት መብለጥ እንዳለበት ነው። የህዝብ የኑሮ ደረጃ መሻሻል ማለት በገቢ አንፃር ከአምናው ከፍ ያለ መሆን ይኖርበታል። የዘንድሮ ገቢ ከአምናው ጋር እኩል ከሆነ የዘንድሮ ኑሮው ከአምናው ጋር ተመሳሳይ ይሆናል። የዘንድሮው ገቢ ከአምናው ካነሰ የዘንድሮ ኑሮው ከአምናው ያነሰ ይሆናል። የዘንድሮው ገቢ ከአምናው ከበለጠ የተሻለ ይሆናል።

የህዝብ ብዛት ለኢኮኖሚ እድገት ጠቃሚ ነው። የህዝብ ብዛት ማለት የአምራች ኃይል እድገት በመሆኑ ሰው ሁሉ ከሰራ ምርቱም በዚያን መጠን ያድጋል ማለት ነው። በአንፃሩም የህዝብ ዕድገት ማለት ብዙ ሸማች ስለሚኖር ለምርት ያለውን ፍላጎት

ያሳድጋል:: ይህም ለአምራቾች ገበያ ስለሚፈጥር ብዛት ያለው ምርት እንዲመረት ግፊት ይፈጥራል:: የህዝብ ብዛት ለኑሮ እድገት ደንቃራም ሊሆን ይችላል:: ሕዝብ እየበዛ ሲሄድ የምግብ ፍላጎት ይጨምራል:: ይህንንም ፍላጎት ለማርካትና በምግብ እራስን ለመቻል በብዛት መመረት ይኖርበታል:: ያለው የእርሻ መሬት ምርታማነት እድገ ይህን ተጨማሪ የምግብ ፍላጎት ካላሟላ አዲስ መሬት መታረስ ይኖርበታል:: ይህም የደን መመንጠርን ያስከትላል:: የደን መመንጠርም የአካባቢውን አየር በመለወጥ ከፍተኛ ሙቀትና የዝናብ እጥረት ብሎም ድርቅ ከማስከተሉ ባሻገር የአፈር መሸርሸርንና ከዚያም አካባቢውን ወደ በረሃ ሊለውጥ ይችላል:: ህዝብ ሲበዛ ለሰው፣ ለእርሻና ለከብት መሆን የውሃ ፍላጎት ይንራል:: ዕድሜው ለሥራ የደረሰ ህዝብ እየበዛ ሲሄድ በዚያው ልክ የስራ መስክም መፈጠር ይኖርበታል:: በህዝብ ብዛት የሚፈጠረው አምራች ኃይል ምርትን ሊያሳድግ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ተመቻችተውለት በምርት ሥራ ላይ ሲሰማራ ብቻ ነው:: እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች መሰረታዊ የኢኮኖሚና ብሎም የማህበራዊ ችግሮች ምንጭ እያደገ የሚሄደውን አምራች ኃይል ወደ ምርት ተግባር እንዲሰማራ የሚያስችል አቅም ውስንነትና የሁኔታዎች አለመመቻቸት ነው::

## መ. የኢትዮጵያ ህዝብ

በ1987 ዓመተ ምህረት በተደረገው ሁለተኛው አገር አቀፍ የህዝብና የቤት ቆጠራ መሰረት በዚያን ዓመት በኢትዮጵያ ይኖራሉ ተብለው የተደረሰበት የህዝብ ብዛት 53,132,253 ነበር:: ከነዚህም ውስጥ 29.9 ሚሊዮኑ ወይም 55.2 በመቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕድሜው ከ20 ዓመት በታች ሲሆን፣ 1.9 ሚሊዮን ወይም 3.5 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከ65 ዓመት በላይ ነው:: ዕድሜአቸው ከ20 ዓመት በላይና ከ65 በታች የሆኑት 21.0 ሚሊዮን ወይም 42.9 ከመቶ ናቸው:: እነዚህም ግለሰቦች በ10.8 በተሰብ ተሰባስበው ይኖራሉ::

በ1994 ዓመተ ምህረት 65.3 ሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ በኢትዮጵያ ይኖራል ተብሎ ይገመታል:: ከዚህም ውስጥ 32.8 ሚሊዮን ተባዕታይና 32.5 አንስታይ ናቸው:: ከመኖሪያ አካባቢ 9.9 ሚሊዮን (4.9 ሚሊዮን ተባዕታይና 5 ሚሊዮን አንስታይ) ወይም

15.2 ከመቶ የሚገመቱት ከተሜዎች ሲሆኑ 55.4 ሚሊዮን ( 27.9 ሚሊዮን ተባዕታይና 27.5 ሚሊዮን አነስታይ) በገጠር ይኖራሉ:: ከዕድሜ አንጻር ሲታይ 35.9 ሚሊዮን ወይም 55 ከመቶ የሚሆነው ዕድሜው ከ20 ዓመት በታች ነው:: 4.4 ሚሊዮን ወይም 6.8 ከመቶ የሚሆነው ዕድሜው ከ55 በላይ ነው:: 25 ሚሊዮን ወይም 38.2 ከመቶ የሚሆነው ህዝብ ዕድሜው ከ20 በላይና ከ55 በታች ይገመታል:: በመሆኑም ኢትዮጲያ ልጆች አገር ነች:: ከ30 ዓመት በኋላ የኢትዮጲያ ህዝብ ከ118 ሚሊዮን ዕስከ 150 ሚሊዮን ሊደርስ እንዲችል ይገመታል:: በአገራችን ያለውን የጤና በተለይም የኤችአይቪኤድስን ስርጭትና ይህም በህዝብ ብዛት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጲያ ህዝብ ቁጥር ከ100 እስከ 120 ሚሊዮን ሊደርስ ይችላል::

## ሰ. ስራ አጥነት

በኢትዮጵያ እድሜው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነውሁሉ ለስራ በቁ[illegible]ቸው ተብሎ ይታሰባል:: በ1994 ዓ.ም. እድሜያቸው ለስራ አቅቷቸዋል የተባለው ህዝብ 44.7 ሚሊዮን ነው:: ከዚህ ውስጥ 32.4 ሚሊዮን የሚሆኑት ስራ ላይ ነበሩ ወይም ስራ ፈላጊዎች ናቸው:: እነዚህም በኢኮኖሚው ውስጥ ተሳተፎ አድራጊዎች ናቸው ማለት ነው:: ከነዚህ ተሳታፊዎች መካከል ምን ያህሉ ሥራ አላቸው ምን ያህሉ ሥራ አጥ ነው የሚለ መረጃ የለም በእምነትና አንዳንድ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ ተሳትፎ ካላቸው ውስጥ ወደ97 ከመቶ የሚሆነው ሥራ አጥ ነው ይባላል::

ይህ ቁጥር የተደረሰበት የገጠሩ ህዝብ በሙሉ ሥራ ላይ ያለ ነው:: ስለዚህም ገጠር ሥራ አጥ የለም በሚል ግምት ሲሆን በከተማ ካለው ህዝብ 20 በመቶው ሥራ አጥ ነው ሚሉ ጠቋሚ ጥናቶች በመነሣት ነው:: የከተማ ነዋሪው ህዝብ ትንሽ ስለሆነ ሥራ አጡም ከአጠቃላይ ህዝብ ትንሽ ይሆናል::

## ረ. የኑሮ ሁኔታ

የኢትዮጵያ ህዝብ ደሃ ለመሆኑ ቁጥር ጠቅሰን ማመሳከር አያስፈልግንም:: መነሻችን ድኅነታችንን አምነን ይኅንኑ ለመቀነስና ብሎም ለማጥፋት ቆርጦ መስራት ነው:: ሆኖም ሙያው የሚፈልግብንን ግዴታ ለሟሟላት አሃዝ ተጠቅመን ስለኑሮ ሁኔታችን አንዳንድ መገለጫዎችን እናሳያለን:: ስለድህነታችን ሰፋ ያለ መግለጫ ከዘህ ጋር በተያያዘ ስልጠናና ለዙሁ ከተዘጋጀላችሁ ጽሁፍ ስለምታገኙ በዚህ ክፈለጊዜና በዚህ ወረቀት የጎላ ትኩረት አንሰጠውም::

በ1994 ዓመተምህረት ይገኛል ተብሎ በመንግስት የተገመተው ምርት ብር 61.8 ቢሊዮን ነው:: ይህ ግምት ዕውን ከሆነ የኢትዮጲያውያን የነፍስ ወከፍ ገቢ በአመት ብር 946 ይሆናል:: ይህ በቀን ብር 2.59 መሆኑ ነው::

ምናልባት ይህ ገቢ በጣም ትንሽ ነው:: እንዴት ሰው በዚህ ገቢ ይኖራል ብላችሁ ብታስቡ አይገርምም:: እንደምታስቡትም በቂ አይደለም:: የሚገርመው ግን ይህ ገቢ የተሰላው ከእውነት በራቀ ታሳቢ ላይ ተመስርቶ ነው:: ይህም ኢትዮጲያውያኖች በአመቱ የተመረተውን ምርት እኩል ቢካፈሉ ለያንዳንዱ ሰው ምን ያህል ይደርሰዋል በማለት የተሰላ ነው:: ግን ይህ እንዳልሆነ ሁላችንም እናቃለን:: የገቢ ልዩነት በመኖሩ:: ነጋዴው በትርፍ፤ ተቀጣሪው ሰራተኛ በደመወዜ ገቢው ከዚህ የበለጠ መሆኑ የታወቀ ነው:: በመሆኑም የአመት፣የወር እንዲሁም የቀን የነፍስ ወከፍ ገቢአቸው ከዚህ ትንሽ ነው ካልነው ብር 2.59 በታች የሆኑ ብዙ ኢትዮጲያውያን መኖራቸውን መረዳት አዳጋች አይሆንም::

በ1991/92 ዓ/ምህረት መንግሥት ባደረገው ጥናት መሰረት 45.5 ከመቶ የሚገመት የኢትዮጲያ ህዝብ ያጣና የነጣ ደሃ ነው:: ደሃ ነው ሲባልም ለኑሮ እጅግ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉትን እንደ ምግብ፣ መጠለያና ልብስ የሚገዙበት ገቢ አያገኙም ማለት ነው:: በመሆኑም ጥናቱ በተደረገበት አመት የነበረው የድሃው ብዛት አሁንም አለ ቢባል በ1994 ዓ/ምህረት ወደ 30 ሚሊዮን የሚገመት ህዝብ የተራበ፣ የታረዘና ሜዳ አዳሪ ነው::

በ1991/92 የነበረው የድሆች ብዛት አሁንም ሊኖር ይችላል ያልንበት ምክንያት ድህነት ስር የሰደደ ችግር በመሆኑ በአጭር ጊዜ ብዙ ይቀንሳል ብሎ ለማሰብ አዳጋች በመሆኑ ነው። በዚህም ላይ የ1992/93 የግብርና ምርት እጅግ ጥሩ ቢሆንም ባስከተለው የዋጋ መቀነስ የገበሬው ገቢ ሊቀንስ ይችላል ከሚል ታሳቢም በመነሳት ነው። ዋናው ቁምነገር ምን ያህሎቻችን ደሆች ነን ሳይሆን ፋይዳው ከላይ እንደተጠቀሰው ብዙ ህዝብ ድሃ መሆኑን ተቀብለን ደሀንን ህዝብ እራሱን ከአባዜውና ከፍዳው ነፃ ሊያወጣ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው።

## VI. መረሃግብራዊ መሣሪያዎች

### ሀ. ግቦች

ድህነትን ለማጥፋት አገርን ለማልማት ከመስተዳደሩ የሚጠበቀው ኢኮኖሚው ሚያድግበት ስልት መቀየስና ዋጋን ማረጋጋት ናቸው።

### ለ. ለእድገት ኃይሎች እድገት

የእድገት ኃይሎች ማለትም የሰው እውቀትና ጉልበት፣ የማምረቻ ኃይሎች ዘመናዊነትና ብዛት ለሚመረተው ምርት ወሳኝነት አላቸው። በመሆኑም አንድ ሰው ከድህነት እራሱን የማውጣትና ለመከበርም ኃላፊነቱን ቢሸከምም መስተዳደሩ ግለሰቦች በተናጠልም ይሁን በቡድን ድህነትን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ እንዲያስችላቸው የምርት ኃሎች ሊበራከቱና ሥራ ፈላጊው ቀጣሪ እንዲየገኝ የሚችሉባቸውን ዘዴዎችና ስልቶች ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። በኢኮኖሚው በኩል መስተዳደሩ ያለበት ሓላፊነት ይህ በመሆኑ።

ከፍ ሲል እንደተገለጸው ግለሰባዊ ኢኮኖሚክስ የያንዳንዱን ግለሰብ የመስራት፣ የማምረት የመፍጀት ውሳኔና ሂደት እንዲሁም በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት የሚያጠና ሲሆን አጠቃላይ ኢኮኖሚክስ ኢኮኖሚውን በአገር ደረጃና አገሩ ከውጭው አለም ጋር ያለውን

## ኢኮኖሚ ፅንሰ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ

ኢኮኖሚአዊ ግንኙነት የሚመረምር፣ የሚተነትን፣ የሚያጠናና ብሎም አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ ወዳለ ወይም ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያድግ የሚችልበትን ስርአትና ስልት የሚቀይስ የእውቀት መስክ ነው፡፡

የአጠቃላይ አኮኖሚውን ሁኔታ በዝርዝር ለመረዳት እንዲያመች ከአጠቃላይ አላማና ግብ መጀመር ጠቃሚ ነው፡፡

ድህነትን ለማጥፋት ትልቁና መሠረታዊ ኃላፊነት የወደቀው በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ከድህነት ለመላቀቅና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል የሚችለው በርትቶ በመሥራትና ተግቶ በማምረት ብቻ ነው፡፡ እያንዳንዱ ግለሰብ በተናጠልም ሆነ በሕብረት የሚያደርገው ተግባር ገቢውን ያሳድገዋል፣ ምርትም ይጨምራል፡፡ የደሐው ሕዝብ ብዛት እየቀነሰ ሲሄድ አገር ለማ ያስብላል፡፡ የሐገር ልማት ከሕዝብ የኑሮ ደረጃ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡

እያንዳንዱ ለአቅመአዳም የደረሰ ሰው ገቢውን ለማሳደግ፣ ንብረት ለማፍራትና ባገኘውም ገቢ እንዳሻው እንዲጠቀምበት እንዲችል መስተዳድሩ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ትልቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህ ነው የመስተዳድሩ መሰረታዊ ሐላፊነት፡፡

በዚህ አኳያ የመስተዳድሩ ኃላፊነት ሰፊ፣ ሁሉን አቀፍና ውስብስብም ነው፡፡ በመጀመሪያ የመከላከያ ኃይልን አጠናክሮ ሕዝቡን ከውጭ አጥቂ መከላከል፣ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ በዲፕሎማሲ መስክ ለሐገሪቷ ጠላቶችን ቀንሶ ወዳጆች እንዲበዙላት ከማድርጉም ባሻገር የአገሪቷን ጥቅም ከጦርነት መለስ በሚረጋገጥና ከውጭ ማግኘት የሚገባትንና ማግኘት የምትችለውን ጥቅም መጠበቅና ማራመድ ይኖርበታል፡፡

በሐገር ውስጥ የሕዝቡ ደህንነት ተጠብቆ ያለአንዳች ሥጋትና ችግር ወጥቶ እንዲገባ፣ ሠርቶ እንዲከብር የሚያስችል ሠላምና መረጋጋት መፍጠር አለበት፡፡ ይህ ሁኔታ ካልተረጋገጠ እያንዳንዱ ግለሰብ ከድህነት ለመውጣት፣ ከድህነት ያመለጠውም ሠርቶ ለማግኘት ሐብት ለማፍራት የሚያደርገው ጥረት ይደበዝዛል፡፡ በመሆኑም መስተዳድሩ ሕግና ደንብን ቀርጾ እነዚህን ተግባራዊ በማድረግ ሕዝቡ ፍጹም ሰላምና ፍጹም ደህንነት

ተሰምቶት ያለአንዳች ጥርጣሬና ሥጋት ለሚሠራው ሥራ ትኩረት በመስጠት ምርታማነቱንና ምርትን የሚያሳድግበት ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል።

ይህም ሲሆን ህዝብ በመስተዳድሩ ላይ እምነት ያድርበታል። በደህንነት አካባቢ በተለይ ሊሠመርበትና በአፅንኦት ሊተኮርበት የሚገባው ሠላምና መረጋጋቱ የዕለት ተዕለት ሳይሆን ዘላቂነትን እንዳለው ሕዝቡ ከፍተኛ እምነት ሊኖረው ይገባል። በተለይም ከውጭም ሆነ ከውስጥ መዋዕለ ነዋያቸውን አፍስሰው በተለያየ የሥራ መስክ የማምረት ኃይል ለመገንባትና በዚህም ሂደት የሥራ ዕድል ለመፍጠር ችሎታና ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ሐሳባቸውን ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉት ዛሬ ያወጡት ኃብት በፖለቲካው አለመረጋጋት፣ ወይም በውጭ ዘራፊ በውስጥ ቀማኛ እንደማያጡት ሲያረጋግጡ ብቻ በመሆኑ ነው። በልማት መስክ የተሰማራ መዋዕለ ንዋይ እንደ ንግዱ ሥራ ዛሬ ወጥቶ ነገ ትርፍ ይዞ የሚመጣ ሳይሆን የወጣው ገንዘብ ጥቅሙ በረዥም የጊዜ ሂደት የሚመለስና የሚገኝ በመሆኑ ነው።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትና ከድህነት የመውጣት፣ አገርን ለማልማት ቁልፍ የሆኑ ምቹ ሁኔታዎች ሲሆኑ በኢኮኖሚው በኩል መወሰድ ያለባቸውን መርሐግብራዊ አስተዳደራዊና መሠረቱ ልማታዊ የሆኑትን ቀጥለን እናያለን።

ወደ ኢኮኖሚው መርሐግብር ስንመለስ ከድህነት አዘቅት የመውጣት ኃላፊነት፣ የግለሰቡ ኃላፊነትና ጥረት መሆኑን ተቀብለን፣ ግለሰቡ ሠርቶ ለመብላትና አግኝቶ የመክበር ምኞቱን ለማሳካት የሚያስችለውን መቹ ሁኔታ መስተዳድሩ መፍጠር የሚችልበትን መሣሪያና ዘዴ ቀጥለን እናያለን።

ይህን ምቹ ሁኔታ መስተዳደሩ እንዴት ሊፈጥር ይችላል ለሚለው ጥያቄ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ ይኖርበታል። የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አላማና መርሃግብርን በስድስት ዋናዋና መደቦች ተለይተው ሊታዩ ይችላሉ። እነዚህም፡-

1. የምርት እንዲያድግ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር
2. ሥራ መፍጠርና የሥራ አጥነትን ማስወገድ
3. የምርት ዋጋ መረጋጋት ማስፈን
4. የውጭ ማዛን ከአቅም በላይ እንዳይሆን መከላከል
5. የተመረተው ምርት ፍትሃዊ በሆነ ዘዴ እንዲከፋፈል ማድረግ
6. በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተመጣጠነ ልማት እንዲኖር ማድረግ ናቸው።

እነዚህን መርሃግብሮች ሰፋ አድርገን ከዚህ ቀጥሎ እናያቸዋለን።

## 1. የምርት እድገት እንዲያድግ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር

የአንድ ገር ህዝብ የኑሮ ደረጃ ሊሻሻል ሚችለው የሚመረተው ምርት እያደገ ሲሄድ ብቻ ነው። በአገሩ ከሚኖረው ህዝብ አኳያ በቂ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የማያመርት አገር ወይም እነዚህን ምርቶች ከውጭ ለመሸመት የሚያስችል በቂ አማራጭ የገቢ ምንጭ ከሌለው ድሀ ነው። ደሃ ነው የምንለው ህዝቡ ለህይወት አስፈላጊ ናቸው የሚባሉትን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት አይችልም ማለት ነው። እነዚህ ለህይወት መሰረታዊ ፍላጎት የሚባሉት ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው። ይህም ሊሆን የሚችለው ለአምራቹ ክፍል ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ብቻ ነው።

### ሀ. የዋጋ መረጋጋት

መስተዳደሩ አገር ውስጥ ገበያ ዋጋን የማረጋጋት ሃላፊነት አለበት ይህ የሚያስፈልግበት የተለያየ ምክንያቶች አሉ። እነዚህም:-

ሀ) የህዝቡን የመግዛት ኃይል ለመንከባከብ። ዋጋ ሲጨምር የገንዘብ የመግዛት ኃይል ይጋሸባል። ትናንት አስር ሳንቲም የነበረው የአንድ ዳቦ ዋጋ ዛሬ 20 ሳንቲም ሲሆን የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ይቀንሳል።

ለ) በህዝብ ዘንድ ዋጋ ይንራል የማለትን ዕምነት ስለሚያሳድር ዋጋ ቀደም ሲል ከነበረው በበለጠ ፍጥነት ያሻቅባል። ለምሳሌ የዳቦ ዋጋ ነገ ይጨምራል የሚል

እምነት ከተሰረጸ ሁሉ ሰው ነገና ተነገወዲያ የሚያስፈልገውን ዳቦ ለመግዛት ይሻማል። ይህም የገበያውን ዋጋ የባሰ ያንረዋል።

ሐ) ሰዎች የሚቆጥቡትን በገንዘብ አይዙም። ሰው ለእቃ መግዣ ካልሆነ በስተቀር ገንዘብ የሚባል ነገር አይዙም። ይህም የምርት ኃይሉችን ለመጨመር የሚያስችል ገንዘብ ያሳጣል።

መ) አምራቾችና መወእለነዋይ አፍሳሾች ሃብታቸውን ወደ ምርት ኃይል አይለውጡትም። የነገን ዋጋ ገምተው አትራፊ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ ስለሚያዳግታቸው።

በአጠቃላይ የዋጋ መናር ለኢኮኖሚውም፣ ለፖለቲካውም ለህብረተሰብ እድገትም አደገኛ ነው። ስለዚህም መስተዳደሩ የገበያ ዋጋ እንዳይንር የመከላከያ ዘዴ መፍጠር አለበት።

በአንፃሩም የገበያ ዋጋ መውደቅ የለበትም። የዋጋ መናር ሸማቾችን እንደሚጎዳ፣ የገበያ ዋጋ መውደቅ አምራቾችን ይጎዳና ምርት ወደ መቀነስ ያዘነብላል። የገበያ ዋጋ መናር ብዙ ሰው ጥቂት ምርት ለመግዛት ከመሞከር እንደሚመጣ ሁሉ የገበያ ዋጋ የሚወድቀው ምርት የሚገዛ ሲጠፋ ነው። ይህም ማለት ላለው ገበያ የተመረተው ምርት በዛ ማለት ነው። ይህ ሲሆን አምራች ከማምረት ይገደባል። ሠራተኛ ከሥራ ሊቀነስና የስራ አጡን ብሎም የችግረኛውን ህዝብ ቁጥር ሲያንረውና በዚህም የተነሳ ድህነት ሊፋፋ ይችላል። ዋጋ እንዳይቀንስ የሸማቾች ገቢ እንዲጨምር ማድረግ ነው። ይህም ለስራ አጥ የስራ እድል መፍጠር አልያም መስተዳድሩ እራሱ ገበያ ውስጥ መግባት አለበት።

በተለይ ሊታሰብበት የሚገባው ጉዳይ ሸማቹ ህዝብ ነገ ገቢ እንደሚያገኝ የማያናውጥና የማያጠራጥር እምነት መያዝ አለበት። ነገ ከስራ ልባረር እችላለሁ፣ ነገ ላጣ እችላለሁ ብሎ ከሰጋ በእጁ የያዘውን ገንዘብ አውጥቶ ከመሸመት ይገደባል። ወጪውም እጅግ ለሚያስፈልጉት ጉዳዮች ብቻ ይወሰናል። ይህ ሲሆን ምርት ገበር ያጣል፣ ኢኮኖሚው

እንቅስቃሴ ይዳከማል:: ነገ አገኛለሁ፣ ከሥራ አልባረርም ብሎ ካመነ በእጁ የያዘውን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ተበድሮም ማረውን ይገዛል:: ይህ ለአምራች አበረታች ስለሆነ ምርት ያድጋል:: የስራ መስክ ይሰፋል:: ስራ አጥም ይቀንሳል:: ኢኮኖሚውም ይደምቃል::

## ለ. በኢትዮጵያ የችርቻሮ እቃ ዋጋ እንዴት ይሰላል?

የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ አላማው የኑሮን ውድነት መለካት ነው:: የፍጆታ ሸቀጣሸቀጦች ዋጋ እየናር ከሄደ ኑሮ ተወደደ ማለት ነው:: ዋጋቸው እየወረደ ከሄደ የኑሮ ዋጋ ቀሰ ማለት ነው:: የችርቻሮ ዋጋ ለመለካት ሰዉ ያስፈልገዋል የሚባሉት እቃዎች በሙሉ ይዘረዘራሉ:: ከዚያ ቀጥሎ ከገቢው ምን ያህል ድርሻ ለምን እንደሚያወጣ ይለካል:: በወቅቱ የእነዚህ እቃዎች ዋጋ ከገበያ ይሰበሰባል:: ከዚያም በዚያ ወቅት ያለው ዋጋ በሌላ ወቅት ከነበረው ዋጋ ጋር ይነፃጸራል:: ከዚህም በመነሳት የኑሮ ውድነት ይለካል:: በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ዋጋ የተረጋጋ ነበር:: ይህም ከፍ ብሎ በተሰጠው ሰንጠረዥ ይስተዋላል:: ለናሙና በተሰጡት 3 አመታት አጠቃላይ ዋጋ የጨመረው ከ5 በመቶ በታች ነው:: ይህ አበረታችና በዚሁ መቀጠል ያለበት ነው::

ሠንጠረዥ 4

**አገር አቀፍ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ**

| | 1990 | 1991 | 1992 |
|---|---|---|---|
| ጠቅላላ | 3.6 | 3.9 | 4.2 |
| ምግብ | 4.3 | -6.9 | 6.7 |
| መጠጥ | -1.0 | -3.8 | 1.7 |
| ሲጋራና ትምባሆ | 3.7 | 7.6 | 0.0 |
| ልብስና ጫማ | 3.1 | -4.0 | 0.1 |
| የቤት ኪራይ፡ ውሃ ሓይል የቤት መስሪያ እቃ | 12.9 | 1.2 | -1.7 |
| የቤት እቃ፡ቤት ሠርተኛ ደመወዝ | 3.1 | 3.7 | 2.0 |
| ህክምና | 9.0 | -10.4 | -2.5 |
| ትራንስፖርትና መገናኛ | 2.1 | 5.1 | 25.6 |
| መዝናኛና ትምህርት | 0.2 | -6.1 | 0.0 |
| የግል ንጽህና | -1.1 | -.1 | -1.2 |
| ሌሎች | 25.0 | -11.0 | 6.3 |

ምንጭ፡- ብሄራዊ ባንክ::

## ሐ. የገበያ ዋጋን ለማስፈን ምን መደረግ አለበት

የገበያ ዋጋ የሚጨምርበት መሰረታዊ ምንጭ ምርት ገዥዎች በሚፈልጉት መጠን ያለመመረት ነው:: ሌሌ ትርጉም የለውም:: በኢኮኖሚው ውስጥ የሚንሳፈፈው የገንዘብ ብዛት የዋጋ መናርን ያስከትላል የሚባለውም ዞሮ ዞሮ ከዚያው ከምርት ጋር የተየየዘ ነው:: ገንዘብ ሲበዛ ምርትም ከበዛ የዋጋ ንረት አይመጣም:: የምርት እጥረት የዋጋ ንረትን የሚያስከትል ከሆነ መፍትሄው ምርትን ማሳደግ ብቻ ይሆናል::

እንደኛ ሥራ አጥ በሞላበት ገር የዋጋ ንረትን ለማርገብና ገበያውን ለማርጋት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚነሳፈፈውን ገንዘብ ቀንሱ ማለት ትክክል አይዶለም:: በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ገንዘብ መቀነስ ማለት በሌላ በኩል በእሳት ላይ ቤንዚን እንደመጨመር ይቆጠራል:: ምክንያቱም የገንዘብ አቅርቦት መቀነስ ማለት በኢኮኖሚወ ውስጥ የሚዘዋወረውን ገንዘብ መቀነስ ነው:: ይህ ሲሆን የገንዘብ ዋጋ ማለትም ወለድ ይንራል:: ይህም የምርት ሂደቱን ያዛባል:: ሰዎች ከባንክ ገንዘብ ተበድረው ለልማት ሥራ ማዋለቸው ቀርቶ ያለውንም የማምረት ኃይል በቅጡ አይጠቀሙበትም:: ሠራተኛ ይባረራል:: በዚህም የተነሳ የምርት እጥረት ይባባሳል:: ያለው እየናረ በሚሄድ ዋጋ እየሸመተ ይበላል::የሌለውስ? እንዲህ አይነቱ መፍትሄ ተበዬ መርሃግብር አደገኛ ነው::

ይህን ለመረዳት በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን ምስል ይመልከቱ:: ከ ሀ ወደ ለ የሚሄደው መስመር የምርት ወሰን ይባላል:: ይህ ማያሳየው ያለንን ለሥራ የተዘጋጀ ሰራተኛ፣ የተፈጥሮ ኃብት፣ ፋብሪካ ወዘተን አሁን ባለን እውቀት በሙሉ ኃይል ተጠቅመን ልናመርት የምንችለው ምርት ነው:: ይህም መስመሩ ላይ ያስቀምጠናል (ለምሳሌ እንደነጥብ ሠ ማለት ነው):: ከዚህ በላይ ልናመርት አንችልም:: ከዚህ በታች ልናመርት እንችላለን:: ይህ ሲሆን ግን የማምረት አቅማችንን ሙሉ በሙሉ አልተጠቀምንበትም ማለት ነው:: ይህም እንደ ነጥብ ረ ወይም ሸ ላይ ያስቀምጠናል ማለት ነው::

መስመር በሀ በግብርናው ዘርፍ ልናመርት የምንችለውን ሲያሳይ፣ መስመር በለ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ልናመርት የምንችለውን ያሳያል። አገሪቷ ነጥብ ሀ ላይ ብትገኝ የምርት ኃሎቻችንን በሙሉ በግብርና ላይ አውለን በሀ ምርት ስናመርት ምንም የኢንዱስትሪ ምርት አናመርትም ማለት ነው። የኢንዱስትሪ ምርት የማናመርተው ምንም የሰውም ሆነ የመሳሪያ ኃይል ለዚያ ተግባር ባለማዋላችን ነው። በአናፀሩ ያለንን የማምረት ኃይላችንን በሙሉ በኢንዱስትሪ ምርት ላይ ብናውል በለ የሚሆን የኢንዱስትሪ ምርት ስናመርት የግብርናው ምርት ግን ምንም አይኖርም። ከ ሀ እስከ ለ ባለው መስመር ላይ ስንሆን የግብርናውም የኢኒዱስሪውም ምርት እናመርታለን። ምክንያቱም የምርት ኃይላችንን በሁለቱም ስላሰማራን።

ከየትኛው ምን ያህል ምርት ይገኛል? ይህን የሚወስነው ሁለቱን ምርት ለማምረት እንዳከፋፈልነው የምርት ኃይል ይሆናል ማለት ነው። ለምሳሌ ነጥብ ሠ ላይ ብንሆን የምርት ኃይሎቻችንን በነዚህ ሁለት ተግባራት ላይ አሰማርተን የሁለቱንም ምርት እኩል አመረትን ማለት ነው።

ኢትዮጵያ በእንደዚህ የምርት ድንበርና ክፍፍል ላይ የት ትገኛለች? በአገራችን በተለይም በከተማው ብዙ ሥራ አጥ በመኖራቸው፣ ምንልባትም ለርሻ ምቹ የሆነ ያልታረሰ መሬት ወይም በምርት ሥራ ላይ ሊውል የሚችል የገንዘብ አቅም ካለንና በሥራ ላይ ስላላዋልነው የምንገኘው በ ሀለ መስመር ላይ ሳይሆን ወደውስጥ ገባ ብለን ነው። ምክንያቱም ያለንን የምርት ኃይል ሙሉ በሙሉ ተጠቅመን ስላላመረትን። በሌላም በኩል የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከኢንዱስትሪው ይልቅ ወደ ግብርናው ስለሚያደላ ከ በሠ መስመር በስተግራ እንደ ነጥብ ሸ ላይ ልንሆን እንችላለን ማለት ነው። ከየትኛው ምርት ምን ያህል እናምርት የሚለውን የሚወስነው ፍላጎታችንና ምኞታችን ሳይሆን በአብላጫው ባለን የማምረት አቅም ይወሰናል።

በአሁኑ ጊዜ ወደ ግብርናው ያደላነው ያለን የምርት ኃይል ወደዚያ ያዘነበለ በመሆኑ ነው። ፈጣንና ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ እድገት ለማስመዝገብ ኢኮኖሚአችንን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ማሸጋገር የግድ ነው። ወደ ኢንዱስትሪ ምርት ለመሸጋገር

ያለንንና ከውጭም ያገኘነውን ጉሉ በኢንዱስትሪ ላይ ማዋል ይኖርብናል:: ይህ ሊሆን የሚችለው በመጀመሪያ ለዚህ የሚሆን መዋዕለ ነዋይ መሰብሰብ ይኖርበታል:: ለኢንዱስትሪም የሚሆን የተማረ የሰው ኃይል ማደራጀት አለብን:: በመሆኑም ይህ በአንድ ጀምበር የሚሆን አይደለም:: የርሻውን ክፍል ማጠናከርና በትጋት መስራት ያስፈልጋል:: ለዚህም የግሉ ክፍል መጠናከርና የግሉ ክፍል ሊሰራ በማይችለው ግን ለአገር እድገትና ልማት በሚያስፈልግ ተግባር የመስተዳድሩ ተሳትፎ እጅግ ወሳኝ ናቸው::


መስተዳድሩ የኢኮኖሚ እድገትን አስፍኖ ድህነትን ለማጥፋት ካሉት ኢኮኖሚው ላይ ከሚያነጣጥሩ መሣሪያዎች መካከል የገንዘብ፣ የውጭ ንግድ፣ የበጀት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: እነዚህን ቀጥለን እናያቸዋለን::

## VII የገንዘብ መረሃግብር

ገንዘብ ማለት አንድን እቃ ለመግዛት የሚያገለግል መሳሪያ ነው:: ይህ መሳሪያ ከሌለ ንግድ የሚካሄደው እቃን በእቃ በመለወጥ ነው:: ይህም አሰራር አድካሚ፣ አሰልችና ጊዜ አባካኝ ነው:: በዚህ ሁኔታ የሚደረግ ንግድ ቅልጥፍና ይጎድለዋል:: በግ ያለው ሰው ኮት ከፈለገ በግን በኮት ለመለወጥ የሚፈልግ ሰው ማግኘት አለበት:: ሁለቱ ከተገናኙ በኋላ በግ ፈላጊው የተገኘው በግ በመልክም በስባትም በልክም እሱ የሚፈልገው መሆን ይኖርበታል:: በአንፃሩም ኮት የሚፈልገው ሰው በበጉ ለውጥ የቀረበለት ኮት የሚፈልገው መሆን ይኖርበታል:: ከዘህ ውስብስብና አስቸጋሪ የንግድና የልውውጥ ሂደት ለመገላገል ግንዘብ ተፈጠረ::

የእቃዎች ልውውጥና ንግድ በገንዘብ አማካኝነት ሲደረግ በግን በኮት ለመለወጥ የሚፈልግ ሰው በጉን በገንዘብ ለውጦ ከዚህ ባገኘው ገንዘብ የፈለገውን ኮት አማርጦ ለመግዛት ያስችለዋል:: ከዚህም ሌላ የበጉና የኮቱ ወጋ የሚለያይ ከሆነ ልዩነቱን በገንዘብ ይወስዳል::

## የምርት ወሰን




ሌላው የገንዘብ ጥቅም የመግዛት አቅም ማካበቻ መሆን ነው:: ገንዘብ ያለው ሰው ገንዘቡን እንዳገኘ በሌላ እቃ መለወጥ የለበትም:: በባንክም ሆነ ትራስ ስር አስቀምጦ ባሻው ጊዜ ለፈለገው ነገር መግዣ ሊጠቀምበት ይችላል::

ማንኛውም ነገር እንደገንዘብ ሊያገለግል የሚችለው ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ሲሟሉ ነው:: እነዚህም አንደኛው አቅርቦቱ ወይም በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ገንዘብ ብርቅ ሆኖ ተፈላጊነቱ እንዲጨምረ ብዛቱ ውሱን መሆን ይኖርበታል:: እንደገንዘብ የሚያገለግለው ነገር እንደአፈር ከሞላ ተፈላጊነቱ ዕጅግ ይቀንሳል:: ብርቅ እንዲሆን ሲባልም ከሚፈለገው በታች ከሆነ ይህም ችግር ነው:: በመሆኑም ከሚፈለገው ሳያንስና ከሚፈለገው ሳይበዛ ኢኮኖሚው ያስፈልገዋል በሚባለው ልክ መሆን ይኖርበታል:: ይህንንም የሚወስነው ብሔራዊ ባንክ ነው::

### ሀ. የገንዘብ አቅርቦትና ምንጭ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ውስጥ በየጊዜው የናኘውን የገንዘብ ልክ ለናሙና ያክል ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ተከቷል::

ሰንጠረዥ 5
የገንዘብ አቅርቦት
(ሚሊዮን ብር)

| | 1990 | 1991 | 1992 |
|---|---|---|---|
| ሀ. ከባንክ ውጪ ያለ ገንዘብ | 4720.0 | 4163.2 | 4881.1 |
| ለ. በተንቀሳቃሽ ሂሳብ ባንክ ተቀማጭ | 6325.8 | 6182.5 | 7133.0 |
| ሐ. ጥሬ ገንዘብ (የሀና የለ ድምር) | 11045.8 | 10345.7 | 12014.1 |
| መ. በማይንቀሳቀስ ሂሳብ ባንክ ተቀማጭ | 7556.5 | 8027.7 | 9121.5 |
| ቁጠባ ሂሳብ | 6481.7 | 7167.4 | 8323.5 |
| የጊዜ ወሰን ሂሳብ | 1074.8 | 860.3 | 798.0 |
| ሠ. አጠቃላይ ገንዘብ (የሐና የመ ድምር) | 18602.3 | 18373.4 | 21135.6 |

ምንጭ:- ብሔራዊ ባንክ::

ሰኔ 30 ቀን 1990 ዓመተምህረት በኢትዮጲያ ሲንቀሳቀስ የነበረው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን 18ቢሊዮን 602 ሚሊዮን 300 ሺ ብር ነበር:: በአንፃሩ ሰኔ 30 ቀን 1992 ዓመተ ምህረት የነበረው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን 21 ቢሊዮን 135 ሚሊዮን 600 ሺ ነበር::

### ይህ ገንዘብ በምን ሁኔታ በሰው ዕጅ ተያዘ ወይም ተቀመጠ?

ሰኔ 30 ቀን 1992 ዓ/ምህረት በህዝብ እጅ ከነበረው አጠቃላይ ገንዘብ ውስጥ 4 ቢሊዮን 881 ሚሊዮን 100 ሺ የሚሆነው ከባንክ ውጪ በሰዎች እጅ የነበረ ገንዘብ ነበር:: ይህ ማለት ሰው በኪሱ ይዞት የነበረው ወይም እቤቱ ያስቀመጠው ሳንቲምና ብር ማለት ነው:: 7 ቢሊዮን 133 ሚሊዮን ብር ደግሞ ባንክ በተንቀሳቃሽ ሂሳብ ወይም በቼክ በሚንቀሳቀስ ሂሳባቸው ውስጥ ግለሰቦች ያስቀመጡት ገንዘብ ነበር:: የነዚህ ሁለት ይዞታዎች ድምር 13 ቢሊዮን 50 ሚሊዮን 300ሺ ብር ይሆናል:: ይህ ገንዘብ ጥሬ ገንዘብ ይባላል:: ምክንያቱም በነዚህ የገንዘብ አይነቶች አንድ ሰው ገበያ ወጥቶ የፈለገውን ዕቃ

ሊሸምት ስለሚችል ነው። አንድ ዕቃ ሲገዛ ሰውየው እኪሱ ባለው ገንዘብ ወይም በቼክ ሊከፍል ይችላል።

ከነዚህ ውጪ ያለውን ገንዘብ ሰዎች ባንክ በማይንቀሳቀስ ሂሳባቸው ውስጥ ያስቀምጡታል። የማይንቀሳቀስ ሂሳብ የተባለው ባንክ ውስጥ በቼክ ከሚንቀሳቀስ ሂሳበ ለመለየት እንጂ አይንቀሳቀሱም ለማለት አይደለም። የማይንቀሳቀስ ሂሳብ ውስጥ በባንክ የሚቀመጥ ገንዘብ ሁለት አይነት ነው። አንደኛው የቁጠባ ሁሳብ ሲሆን ይህም በባንክ ገንዘብ የሚያስቀምጥ ሰው በአብዛኛው የሚጠቀምበት ነው። ይህ ገንዘብ የማይንቀሳቀስ የተባለበት ምክንያት ባለ ሂሳቡ የያዘው ገንዘብ ሳይሆን ባንክ ገንዘብ እንዳለውና ምን ያህል እንዳለው የሚገልጽ ደብተር ነው። አስቀማጩ ገንዘብ ከፈለገ ባንክ ሄዶ ገንዘብ ማውጣት አለበት።

ሁለተኛው የማይንቀሳቀስ ሂሳብ የሚባለው በጊዜ ገደብ ባንክ የሚቀመጥ ገንዘብ ነው። ይህም ለአንድ ጉዳይ ለምሳሌ ቤት ለመስራት አንድ ሰው ገንዘቡን ያስቀምጣል። በጊዜ ገደብ ከሚያስቀምጥባቸው ምክንያቶች አንዱ ገንዘቡን ካሰበው አላማ ውጭና ጊዜ ለሌላ ነገር እንዳይጠቀምበት እራሱን መቀየጃ ዘዴ መሆኑ ነው። ሰኔ 30 ቀን 1992 ዓ/ምህረት በዚህ በጊዜ ገደብ ባንክ አስቀምጠው የነበረው ገንዘብ 798 ሚሊዮን ብር ነበር።

## ሰ. የገንዘብ ምንጭ

የገንዘብ ምንጭ የአገሩ መእከለዊ ባንክ ነው። በኛ አገር የኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክ ነው። ይህም ባንክ የኢትዮጵያ ገንዘብ ቋት ወይም የገንዘብ ጎተራ ነው። ታድያ ከዚህ ጎተራ ገንዘብ እንዴት ይወጣል?

የኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክ ለመንግስት ባንክ ነው። ግለሰቦች በዚህ ባንክ ገንዘብ ለማስቀመጥም ሆነ ለመበደር አይችሉም። ክልክል ነው። ለመንግስት እንደባንክ ስለሚያገለግል መንግስት ያለውን ገንዘብ በዚህ ባንክ ያስቀምጣል። ለመንግስት ባንክ እንደመሆኑ ሲቸግረው ገንዘብ ከዚህ ባንክ ወይም በዚህ ባንክ በኩል ይበደራል። ግን ሲቸግረው ወይም ሲፈልግ ያሻውን ያህል ሊወስድ ወይም ሊበደር አይችልም። ሊበደር

የሚችለው የተወሰነ መጠን ነው፡፡ ስለዚህ አንዱ ገንዘብ ከብሄራዊ ባንክ የሚወጣበት መንገድ ለመንግስት በማበደር ይሆናል፡፡ መንግስትም የተበደረውን ገንዘብ ለሚገዛቸው እቃዎችና ለቀጠራቸው ሰዎች ደሞዝ ሲከፍል ከብሄራዊ ባንክ የወጣው ገንዘብ ግለሰቦች እጅ ይገባል ማለት ነው፡፡

ብሄራዊ ባንክ የንግድና የልማት ባንኮችም ባንክ ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህ ድርጅቶች ገንዘብ ያስቀምጡበታል፡፡ ሲቸግራቸውም ያበድራቸዋል፡፡ እነዚህም ባንኮች ከብሄራዊ ባንክ የተበደሩትን ገንዘብ ለግለሰቦች ሲያበድሩና የተበደሩትም ሰዎች ለእቃ መግዣና ለቀጠሩት ሠራተኛ ደሞዝ ሲከፍሉ ገንዘቡ ግለሰቦች እጅ ይደርሳል ማለት ነው፡፡ ገንዘብ ከብሄራዊ ባንክ የሚወጣበት ሁለተኛው መንገድ ይህ ነው፡፡

ብሄራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ማለትም ተቀባይነት ያላቸው የውጭ አገር ገንዘቦች ብቸኛ ጎተራ ነው፡፡ በህጉ መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ አገር ገንዘብ መንግስትም ሆነ ግለሰቦች መያዝና ማስቀመጥ ክልክል ነው፡፡ ግለሰቦችና መንግስት ለሚያስፈልጋቸውና ለተፈቀደላቸው ጉዳይ የሚያስፈልጋቸውን የውጭ አገር ገንዘብ ከብሄራዊ ባንክ ወይም እሱ ከወከለው መግዛት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም መንግስትም ሆነ ግለሰብ ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ ለብሄራዊ ባንክ የመሸጥ ግዴታ አለባቸው፡፡ ብሄራዊ ባንክም የውጭ አገር ገንዘብ፣ ለምሳሌ እንደ የአሜሪካን ዶላርና የመሳሰሉትን ሲገዛ ለሻጮቹ ብር ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም ገንዘብ ከባንክ የሚወጣበት ሦስተኛው መንገድ ነው፡፡

ብሄራዊ ባንክ ለተለያዩ ጉዳዮች የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለምሳሌ ለሠራተኛ ደመወዝ፣ ለጽህፈት መሣሪያ ወዘተ ለመግዛት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከራሱ አውጥቶ ይገዛል፡፡ ይህም ገንዘብ ከብሄራዊ ባንክ የሚወጣበት አራተኛው መንገድ ነው፡፡

በነዚህ መንገዶች ዕስከ ሰኔ 30 ቀን 1992 ዓ/ምህረት ድረስ ከብሄራዊ ባንክ የወጣው ገንዘብ 5 ቢሊዮን 311 ሚሊዮን 900 ሺ ብር ነው:: የህም በወጣበት ገንዘብ አይነት ልክ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ተዘርዝሯል::

ሰንጠረዥ 6

እስከ ሰኔ 30፣ 1992 ከብሄራዊ ባንክ የወጣ ገንዘብ በአይነት

(በሚሊዮን ብር)

| የብር ዓይነት | | | | | | የሳንቲም አይነት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 5 | 10 | 50 | 100 | 1 | 5 | 10 | 25 | 50 |
| መጠን | 216.7 | 113.6 | 1113.0 | 780.1 | 2988.3 | 0.6 | 18.7 | 43.8 | 15.4 | 21.7 |

ምንጭ:- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ::

## ሐ. ባንኮችና ገንዘብ የመፍጠር ችሎታቸው

በሰንጠረዥ እንደተገለጸው ሰኔ 30፣ 1992 ዓ/ምህረት በአገራችን የነበረው ገንዘብ አቅርቦት ወይም የነበረው ገንዘብ ብር 21.1 ቢሊዮን እንደነበር ታይቷል። ነገርግን በአገራችን በቸኛ ከሆነው ከብሄራዊ ባንክ የወጠው ገንዘብ በአጠቃላይ ብር 5.3 ቢሊዮን መሆኑ ተገልጧል:: ልዩነቱ ከየት መጣ?

የዚህ ሚስጢር ያለው በንግድና ልማት ባንኮች አሰራር ነው

ባንኮች የራሳቸው ገንዘብ የላቸውም:: ሥራቸው ግን ገንዘብ ማበደር ነው:: ይህንን ተግባራቸውን ለመወጣት ገንዘብ በተራቸው ይበደራሉ:: ለባንኮች ዋናውና መሰረታዊው የገንዘብ ምንጮች ከገቢአቸው ላይ ቆጥበው በአደራ መልክ እነሱ ዘንድ ገንዘባቸውን የሚያስቀምጡ ግለሰቦችና ድርጅቶች ናቸው:: ባንኮች ከነዚህ ሰዎችና ድርጅቶች ለተበደሯቸው ገንዘብ ወለድ ይከፍላሉ:: ባንኮችም በተራቸው ከግለሰቦችና ከድርጅቶች ያሰባሰቡትን ገንዘብ በተራቸው ያበድራሉ:: የሚያበድሩትም ለአበዳሪዎቻቸው ከሚከፍሉት ወለድ በለይ ነው:: በተበደሩበትና ባበደሩበት ወለድ መካከል ያለው ልዩነት ወጪአቸውን ቶሎ የትርፍ ምንጫቸው ይሆናል::

ከግለሰቦችና ከድርጅቶች በአደራ የሰበሰቡትን ገንዘብ መልሰው በማበደር የንግድና የልማት ባንኮች ገንዘብ ይፈጥራሉ:: ይህንን በምሳሌ ለመረዳት አቶ በቀለ ብር 100 አቢሲኒያ ባንክ አስቀመጡ እንበል:: አሁን አቶ በቀለ ብር 100 ለአቢሲኒያ ባንክ አበደሩ ማለት ነው:: ለዚህም ባንኩ በየአመቱ በመቶ ብር 6 ብር ወለድ ይከፍላቸዋል:: አቶ ተስፋዬ ብር 100 ያስፈልጋቸውና ወደ አቢሲኒያ ባንክ ሄደው ይበደራሉ:: ከዚህ ድርጊት በኋላ የለውን ገንዘብ መጠን ተመልከቱ:: አቶ በቀለ 100 ብራቸውን ባንክ ከማስገባታቸው በፊት እሳቸው በኪሳቸው ብር 100 ነበራቸው:: አቶ ተስፋዬ ግን ምንም ገንዘብ አልነበራቸውም:: አቶ ተስፋዬ 100 ብር ባንክ ሲያስገቡ የዚያን ያህል ገንዘብ ባንክ አላቸው:: ምንም ገንዘብ ያልነበራቸው አቶ ተስፋዬ ከባንክ ከተበደሩ በኋላ ብር 100 ብር አላቸው:: በመሆኑም 100 ብር ብቻ የነበረው ገንዘብ አሁን ሁለት መቶ ብር ሆነ ማለት ነው:: የአቶ በቀለ 100 ብር ከብሄራዊ ባንክ የወጣ ቢሆን የንግድ ባንኮች ይህንን ገንዘብ ያባዙታል:: በዚህም ሥራቸው ገንዘብ ይፈጥራሉ ማለት ነው::

እስከ ሰኔ 30፣ 1992 ዓ/ምህረት ድረስ ከብሄራዊ ባንክ የወጣውን ብር 5.3 ቢሊዮን የንግድና የልማት ባንኮች ብድር እየሰጡ ወደ ብር 21.1 አባዙት ማለት ነው:: በዚህ ሁኔታ የንግድና የልማት ባንኮች ብር 15.8 ቢሊዮን ፈጥረዋል ማለት ነው::

## መ. ባንኮች ምን ያህል ገንዘብ ሊፈጥሩ ይችላሉ? ምንስ ያህል መፍጠር አለባቸው?

የንግድ ባንኮች ዋናና መሰረታዊ አላማ የቻሉትን ያህል ገንዘብ አበድረው የተቻላቸውን ትርፍ ማግበስበስ ነው:: የተፈጠሩትም ለባለቤቶቻቸው ትርፍ ለማስገኘት እንጂ ለሌላ አላማ አይደለም::

በእንፃሩ የብሄራዊ ባንክ አለማና ተግባር ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለዋጋ መረጋጋት፣ የሥራ እድል በሰፊው እንዲፈጠርና አገር እንድትለማና ይህንንም ለማስገኘት የሚያስችል የገንዘብ መርሃግብር ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ነው::

ኢኮኖሚ ፅንሰ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ

ይህንን ሃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው መንግስት ተገቢውን ስልጣን ሰጥቶታል፡፡ ከስልጣኑም መካከል ገንዘብ የሚወጣበትንና ብድር የሚሰጥበትን ሁኔታ ወለድን መወሰን፤ ውጭምንዛሪ መርሃግብርን መቅረፅና ተግባራዊ ማድረግ፣ የውጭ ምንዛሪን ማስተዳደርና ማደላደል፣ ባንክችንና የመድን ድርጅቶችን መቆጣጠር፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህን ሥልጣናት በመጠቀም ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለዋጋ መረጋጋት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት ጥረት የሚያደርግ መስሪያቤት ነው፡፡

ብሄራዊ ባንክ ኢኮኖሚው እንዲያድግ፣ የገበያ ዋጋ እንዲረጋጋ፤ ሥራ አጥነት እንዲቀንስና በአጠቃላይም አገር ሊለማ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት የሚያደርገው በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረውን የገንዘብ መጠን በሚፈለገው ልክ በማድረግና ወለድን ለቆጣቢዎች የሚጠቅም፣ ገንዘብ ያላቸውም ሆኑ ከባንክ ተበድረው በልማት ተግባር ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉትን ለማበረታታት በሚያስችል መጠን በመወሰን ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ከውጭ ምርቶችን ለማስገባት፤ ለተገኙ አገልግሎትና ለውጪ እዳ ክፍያ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ያቀርባል፡፡

## ሠ. የገንዘብ መጠንን መቆጣጠር

ብሄራዊ ባንክ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወርውን የገንዘብ መጠን እንዴት አድርጎ ነው የሚቆጣጠረው  የሚያስተካክለው ሦስት ዘዴዎችን በመጠቀም ነው፡፡ አንደኛው ባንኮች በአደራ ከሰበሰቡት ገንዘብ ውስጥ የተወሰነውን ያህል ለመጠባበቂያ እንዲያስቀምጡ ማስገደድ ነው፡፡ ይህ በእንግሊዘኛው Reserve Requirement የሚባለው ነው፡፡ ይህ ሁለት አላማ አለው፡፡ አንደኛው ሰዎች ገንዘባቸውን ያስቀመጡበት ባንክ ድንገት ቢከስር ገንዘባቸውን  በሙሉ እንኳን ባይሆን ትንሽ እንዲያገኙ ማድረጊያ መሣሪያ ነው፡፡ ሁለተኛ ውና መሰረታዊው ባንኮች ኢኮኖሚው ከሚፈልገው መጠን በላይ የሆነ ገንዘብ እንዳያበድሩ መግቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ባንኮች በመጠባበቂያ ያስቀመጡትን ገንዘብ ሊያበድሩ ስለማይችሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ብሄራዊ ባንክ በሥራ ላይ ያዋለው የመጠባበቂያ

መጠን 5 በመቶ ነው:: ይህም ማለት አንድ ባንክ ከድንበኛው 100 ብር በአደራ ቢቀበል ሊያበድር የሚችለው 95 ብር ብቻ ነው ማለት ነው:: የዚህ መሣሪያ ቁምነገሩ ይህንን መጠን በፈለገው ጊዜ ከፍና ዝቅ ሊያደርገው መቻሉ ነው:: ይኅን በማድረግ ባንኮች ሊፈጥሩ ሚችሉትን የገንዘብ መጠን ኢኮኖሚው ከሚፈልገው በላይ ወይም በታች እንዳይሆን ያደርግበታል::

ሁለተኛው መሣሪያ ለባንኮች የሚሰጠውን ብድር መቆጣጠር ነው:: ቀደም ሲል እንደተገለጠው ባንኮች የሚያበድሩት ገንዘብ ሲቸግራቸው ከብሄረዊ ባንክ ይበደራሉ:: ታድያ ባንኮች ገበያቸው ደርቶ ከህዝብ በአደራ ያሰባሰቡትን ገንዘብ አበድረው ከሚጠጡ በኋላ ለማበደር ቢፈልጉ ገንዘብ ለማግኘት ወደ ብሄራዊ ባንክ ሄደው ብድር የጠይቁታል:: ብሄራዊ ባንክ የሚያበድራቸው እሱ በሰጣቸው ብድርና ከዚያም ባንኮች በሚፈጥሩት ገንዘብ ኢኮኖሚውን የሚያናጋ አለመሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ነው:: ባንኮች ለሚያቀርቡት የብድር ጥያቄ ብሄራዊ ባንክ ከሁለት አንዱን መልስ ይሰጣቸዋል:: ወይ ያበድራቸዋል ወይ አያበድረቸውም:: ከዚህም ሌላ ካበደራቸው የሚያበድርበትን ወለድ እንደሁኔታው ከፍም ዝቅም ሊያደርገው ይችላል:: ባንኮችን ሊጎታ ከፈለገ የሚያስከፍላቸውን ወለደ ከፍ ያደርገዋል:: ተጨማሪ ገንዘብ ለኢኮኖሚው ይበጃል ብሎ ካሰበ የሚያበድርበትን ወለድ ዝቅ ያደርገዋል:: ወለዱንም ከሚበደሩት ገንዘብ ቆርጦ ነው የሚሰጣቸው:: በዚህ ዘዴ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚንሸራሸረውን ገንዘብ በሚፈለገው መጠን ሊያስተካክል ያስችለዋል:: ይህም በእንግሊዝኛ Discount Rate የሚባለው ነው::

በኢኮኖሚው ውስጥ የሚንሸራሸረውን ገንዘብ ለማስተካከል ብሄራዊ ባንክ ያለው ሦስተኛ ው መሣሪያ የመንግስትን የእዳ ሰነዶች መግዛትና መሸጥ ነው:: የዚህን መሳሪያ አሰራር ለመረዳት መታወቅ ያለበት ብሄራዊ ባንክ ያለ ግንዘብ ገንዘብ አለመሆኑን ነው:: ገንዘብ የምንለው ከብሄራዊ ባንክ ማለትም ከጎተራው ወጥቶ ሰው እጅ ሲገባ ብቻ ነው:: እንደሚታወቀው ምንግስት ገንዘብ ሲቸግረው ከብሄራዊ፣ ከንግድ ባንኮችና ከሌሎችም

ይበደራል። ሲበደርም ዕዳ እናዳለበት፣ ሚከፍለው ወለድና መቼ እንደሚከፍል የሚያረጋግጥ መተማመኛ ለአበዳሪው ይሰጣል። ይህም መንግስት የእዳ ሰነድ የሚባለው ነው። ብሄራዊ ባንክ በኢኮኖሚው ውስጥ ሚንሸራሸረው ገንዘብ አንሶ ከታየው እነዚህን ሰነዶች ከባንኮችና ከሌሎች ሰዎች ይገዛል። ይህን ሲያደርግ ገንዘብን ከጎተራው አውጥቶ በወረቀት በመለወጥ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረውን የገንዘብ መጠን ያሳድጋል። በአንጻሩም በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ገንዘብ በዛ ብሎ ካመን ሰነድ ይሸጣል። ይህን ሲያደርግ ገንዘብ ከኢኮኖሚው ውስጥ ይቀንሳል ማለት ነው። ይህም በእንግሊዝኛ Open Market Operation የሚባለው ነው።

ብሄራዊ ባንክ የኢኮኖሚውን ቅልጥፍናና ዕድገት የሚያግዝበት ሁለተኛው መሣሪያ ወለድ ነው። ወለድ እጅግ ሲንር ሁሉም ገንዘብ አስቀማጭ እንጂ ተበዳሪ አይሆንም። አንድ ሰው ገንዘብ ከባንክ ተበድሮ ፋብሪካ የሚከፍተውና ግብርናውን የሚያስፋፋው ከዚህ ሥራው የሚያገኘው ገቢ ወጪውን ሸፍኖ የባንክ ብድሩን ከነወለዱ ከፍሎ ትርፍ የሚያገኝበት መስሎ ሲታየው ብቻ ነው። ወለድ ከናረ ጉዳት ያመጣል። ሰው ከባንክ ገንዘብ ተበድሮ ለልማት አያውለውም። አንድ ሥራ ሰርቶ ከሚያገኘው ጥቅም ይልቅ ገንዘቡን ባንክ በማስቀመጥ ከላንዳች ውጣ ውረድ ከወለዱ የሚያገኘው ገቢ የተሻለ መስሎ ከታየው በገንዘቡ መስራት ትቶ ባንክ ያስቀምጠዋል። ይህም ለባንኮችም ለአገርም አይበጅም።

ወለድ እጅግ ዝቅ ካለ ሰው ገንዘቡን ባንክ ላያስቀምጥ ይችላል። ሰው ባንክ ገንዘቡን ባንክ ካላስቀመጠ ባንኮች ልማትንና ዕድገትን ለሚያግዙ ሰዎች ሊያበድሩ አይችሉም። ስለዚህ ነው ወለድ ቆጣቢዎችን የሚያበረታታ፣ ተበድረው ወደ ልማት ሥራ ለመግባት የሚፈልጉትን ሰዎች በሚያደፋፍር መጠን መወሰን ያለበት። ብሄራዊ ባንክ ወለድን በዚህ ደረጃ ያስተካክላል።

ሌላው የብሄራዊ ባንክ ችሎታ ባንኮች አገርን ሊጠቅም በሚችልና ቅድሚያ ለሚሰጠው ተግባራት ብቻ እንዲያበድሩ ሊያዝ ይችላ። ለምሳሌ የሸቀጦች እጥረት ሲኖርና ገንዘብ

በጁ ይዞ ያለ ሰው የሚገዛው ምርት እያጣ ባለበት ሁኔታ ባንኮች ለሸቀጥ ሽመታ ቢያበድሩ ውጤቱ ዋጋ ንረት እንደመሆኑ፣ ብሄራዊ ባንክ ባንኮችን የሸቀጥን አቅርቦት ለሚረዱ እንጂ ለሽመታ እንዳያበድሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ብሄራዊ ባንክ ይህን ሁሉ የሚያደርገውና ማድረግም ያለበት ኢኮኖሚውን ለማለማት ዋጋን ለማረጋጋት ገንዘብና ወለድ ከፍተኛ ሚና ስላላቸው ነው፡፡ ይህ እንዴት እንደሆነ ዝቅ ብለን እናያለን፡፡

## ረ. የውጪ ምንዛሪ አቅርቦትና የውጪ ምኒዛሪ ተመን

ከላይ እንደተገለጸው ብሔራዊ ባንክ የውጪ ምንዛሪ ጎተራ ነው፡፡ ከዚህም ጎትራ በየወቅቱ ይለቃል፡፡ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ የሚለቀው፡-

ሀ. የውጭ እዳ ክፍያ

ለ. ለገቢ ንግድ ክፍያ

ሐ. ለአገለግሎት ክፍያ

የውጭ ምንዛሪ ዋጋ የሚተመነው በገበያ ስለሆነ ብሔራዊ ባንክም ሆነ መስተዳድሩ ሊወስኑ አይችሉም፡፡ ብሔራዊ ባንክ የሚያደርገው ያስፈልጋል ብሎ የገመተውን የውጭ ምንዛሪ ለጨረታ ማቅረብ ነው፡፡ የተፈቀደላቸው ፈላጊዎች እርስ በርሳቸው ተጫርተው አቅርቦቱን የጨረሰው ዋጋ የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ሆኖ ስከሚቀጥለው ጨረታ ያገለግላል፡፡

በአገራችን በስራ ላይ የዋለው የጨረታ ዘዴ ደች ጨረታ የሚባለው ነው፡፡ ይህም ገዢዎች አንዱን ዶላር የሚገዙበትን ዋጋና ሚፈልጉትን መጠን ቀደም ብለው ይገልጻሉ፡፡ ፈላጊዎች ያቀረቡት ጥያቄ ባቀረቡተ ዋጋ ከከፍተኛው እስከ ዝቅተኛው ይደረደራል፡፡

የውጭ ምንዛሪ ሽያጭ የሚያካሄደው ከፈተኛ ዋጋ ካቀረበው ጀምሮ የቀረበው የውጭ ምንዛሪ እስኪያልቅ መውረድ ነው፡፡ በመጨረሻ የተሸጠበት ዋጋ ቀረበውን የወጭ

ምንዛሪ ያሟጥጣል፡፡ ይህ የመጨረሻ ዋጋ ነው የውጭ ምንዛሪ ዋጋ የሚሆነው፡፡ የውጭ ምንዛሪ ዋጋ በአሜሪካን ዶላር ይሁን እንጂ ለሁሉም የወጭ ገንዘቦች ያገለግላል፡፡ ይህም የሚሆነው ሌሎች ገንዘቦች ከአሜሪካን ዶላር ጋር የሚመነዘሩበትን ዋጋ በመውሰድ ነው፡፡

ለምሳሌ ዛሬ አንድ ሰው 5000 የጣሊያን ሊሬ ቢፈልግ ወደ ኢትዮጵያ ብር ይህንን ለመመንዘር አንድ ዶላር ስንት ሊሬ እንደሆነ ካወቀ በኋላ ነው፡፡ አንድ ዶላር ብር 8.52 ቢሆንና አንደ ዶላር 2500 ሊሬ ቢሆን አምስት ሺህ ሊሬ ብር 17.04 ይሆናል ማለት ነው፡፡

## IX. የወጪ ንግድና መርሀግብር

ማንኛውም አገር የሚፈልገውን ሁሉ አምርቶ በሁሉም ነገር ራሱን ችሎ ከቀረው አንዳንዱን ምርት ዓለም ራሱን ነጥሎ ሊኖር አይችልም፡፡ ይህንን ለማድረግ ችሎታ ቢኖረው እንኳን ሊያደርግ የሚችለው እጅግ በጣም ውድ በሆነ ዋጋ አምርቶ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች ፍላጎታቸውንና ችሎታቸውን ገምተው በተለያየ የሥራ መስክ ተሰማርተው የተለያየ ምርት አምርተው እንደሚለዋወጡ ሁሉ አገሮችም ይህን የስምሪት ዘዴ በመጠቀም የላቀ ችሎታ ባላቸው ተግባር ተሰማርተው ምርት ያመርታሉ፡፡ ከራሳቸው ፍላጎት ውጪ ያመረቱትን ለሌሎች አገሮች ሸጠው እነሱ ያላመረቱትን ግን የሚያስፈልጋቸውን ምርት ከሌሎች አምራች አገሮች ይሸምታሉ፡፡ ይህም የአለም ገበያንና የአለም የምርት ዋጋን ይፈጥራል፡፡

ኢትዮጵያም እዚህ ቀለበት ውስጥ ያለች ሀገር ነች፡፡ በመሆኑም ችሎታችን፣ አቅማችንና የአየር ንብረታችን የፈቀደውን አምርተን ወደ ወጪ በመሸጥ ከሌሎች አገሮች የሚያስፈልገንን ሸቀጥ እንሸምታለን፡፡

በሥልጣኔና በአቅም ውሱን በመሁናችን የኛ የማምረት አቅም ያጋደለው ወደ ግብርና ምርቶች ነው፡፡ በመሆኑም የወጪ ንግዳችን በግብርና ምርት ላይ አተኩሯል፡፡ በአንፃሩም የገቢ ንግዳችን በኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ያተኩራል፡፡ ይህም በሚቀጥሉት የወጪና የገቢ ንግድ ሰንጠረዦች ይታያል፡፡

ሰንጠረዥ 8
የወጪ ንግድ ምርቶች በአይነት
(በሚሊዮን ብር)

| | 1990 | 1991 | 1992 |
|---|---|---|---|
| ቡና | 2889531 | 2112713 | 2353646 |
| ጥራጥሬና የቅባት እህሎች | 417613 | 373120 | 259852 |
| ቆዳና ሌጦ | 372253 | 347699 | 285461 |
| ጫት | 272355 | 444988 | 618771 |
| ሌሎች | 189830 | 291365 | 440072 |
| ጠቅላላ | 4141582 | 3569885 | 3957802 |

ምንጭ፡- ብሔራዊ ባንክ

ከላይ እንደተገለጠውና ከወጪ ንግዳችን ሰንጠረዥ እንደሚታየው ወደ ውጪ የምንሸጣቸው ምርቶች የግብርና ውጤቶች ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ዋነዎቹ የውጪምንዛሪ ምንጮቻችን 5 ናቸው፡፡ እነዚህም ቡና፣ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬዎች፣ ቆዳና ሌጦና ጫት ናቸው፡፡ እነዚህ አምስት ምርቶች ብቻ 90 ከመቶ በላይ የሆነውን የአገሪቷን የውጭ ምንዛሪ ያመነጫሉ፡፡ ሌሎች ከ 30 የማያንሱ ወደ ውጭ የምንልካቸው ምርቶች የመያመጡት የውጭ ምንዛሪ አገሪቷ በየዓመቱ ከምታገኘው ውስጥ የሚያበረክቱት ከ 10 በመቶ ያነሰ ነው፡፡ በዚህ በኩል ያለው የእድገት ስልት ወደውጭ የምንልካቸውን ምርቶች በቁጥር፣ በብዛትና በጥራት ማቅረብ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተየይዞ የሚታየው ጉዳይ ምርታችንን የት እንደምንሸጥ ነው፡፡ የምርታችን ዋናዋና ተቀባዮች አውሮፓና እስያ ናቸው፡፡ አውሮፓ 54 ከመቶ፣ እስያ 25 ከመቶ ሲገዙ የደቡብና የሰሜን አሜሪካ አገሮች 10 ከመቶ ነው፡፡ በአገር ደረጃ ሲታይ ዋና ዋናዎቹ ገዢዎቻችን ከአውሮፓ ጀርመንና ጣሊያን ከእስያ ጃፓንና ሳኡዲት አረብ ናቸው፡፡ እነዚህ አራት አገሮች ከ 60 ከመቶ የማያንሰውን ምርቶቻችንን ሸማቾች ናቸው፡፡ በአገር ደረጃ አንደኛው ጀርመን ሁለተኛ ጃፓን ሦስተኛ ሳኡዲት አረብ አራተኛ ጣሊያን ሲሆኑ አሜሪካ አምስተኛ ናት፡፡

እዚህ ላይ ሊታሰብ የሚገባው ገበያችንን ማስፋት ጉዳይ ነው፡፡ ወደ ውጭ እንደምንልከው ምርት በአንድ እግር ላለመቆም፡፡ በገቢ ንግድ በኩል ከላይ እንደተገለጠው ከውጭ የምንሸምተው የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ነው፡፡ ዝርዝሩ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ተካቷል፡፡

የገቢ ምርቶችን በአራት ክፍለን ልናያቸው እንችላለን:: እነዚህም ለፋብሪካዎቻችንና ለግብርና የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችና በከፊል የተፈበረኩ ግብአቶች፣ የምርት ኃይላችንን ለመገንባት የሚያስችሉን መሣሪያዎች፣ነዳጅና የፍጆታ ሸቀጦች ናቸው:: በቅደም ተከተላቸው የነዚህ ምርቶች አማካይ ድርሻ 20 ከመቶ፣ 34 ከመቶ፣ 18 ከመቶና 28 ከመቶ ናቸው::

ሰንጠረዥ 9
የገቢ ንግድ እቃዎች በአገልግሎታቸው ዓይነት
(በሚሊዮን ብር)

| | 1989 | 1990 | 1991 |
|---|---|---|---|
| ጥሬ እቃዎች | 173.6 | 191.3 | 203.9 |
| በከፊል የተዘጋጁ እቃዎች | 1629.7 | 1527.1 | 1966.1 |
| ማዳበሪያ | 178.5 | 51.2 | 377.4 |
| ነዳጅ | 1568.5 | 2282.8 | 1329.9 |
| ለምርት አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎች | 3303.3 | 2780.5 | 3945.0 |
| ለግብርና | 85.2 | 66.7 | 111.6 |
| ከባድ መኪናዎች | 789.4 | 478.9 | 886.2 |
| የፍጆታ እቃዎች | 1754.3 | 1839.4 | 3288.4 |
| ዘላቂ የፍጆታ እቃዎች | 828.1 | 784.7 | 1150.5 |
| የቤትና ቀላል መኪናዎች | 292.2 | 292.7 | 402.5 |
| ዘላቂ ያልሆኑ የፍጆታ እቃዎች | 926.2 | 1054.7 | 2137.9 |
| ጥራጥሬ | 15.2 | 53.7 | 492.7 |
| ሌሎች ምግቦች | 92.6 | 136.9 | 261.3 |
| ጨርቃ ጨርቅ | 304.6 | 360.3 | 572.9 |
| ሌሎች | 75.8 | 716.6 | 968.7 |
| የእቃዎች የገቢ ንግድ | 8505.2 | 9337.7 | 11702.0 |

ምንጭ:- ብሄራዊ ባንክ::

ከውጭ የምንገዛዋና የምንሸጠው ሸቀቶችን ብቻ ሳይሆን አገልገሎቶችንም ጭምር ነው:: ኢትዮየጵያ ከምትሸጠውና ከምትታወቅባቸው አገልግሎቶች የውጭ ጉብኚዎችን ማስተናገድና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው:: ከውጭ የምንገዛቸው አገልግሎቶች እጅግ ብዙ ናቸው:: ከነዚህም አማካሪዎች፣የሥራ ተቋራጮች፣ አስተማሪዎች፣ የኢንሹራንስና የባንክ አገልግሎቶችንና ሌሎችንም ይጨምራል::

## X. የውጭ ክፍያ ሚዛንና የውጭ ዕዳ

የውጭ ክፍያ ሚዛን መርሀግብር እውጭዎች የሚያተኩሩበት የአንድን አገር የውጭ ግን ኙነት ሁኔታ የሚያሳይ የመረጃ ሰንጠረዥ ነው፡፡ ከዚህ ሰንጠረዥ በመነሳት ነው የአገሪቷ የውጭ ኢኮኖሚ መርሃግብር የሚነደፈው፡፡

የኢትዮጵያን የሦስት አመት የክፍያ ሚዛን የማያሳይ ሰንጠረዝ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡ የሚከተለው ገለጣ ይህን ተንተርሶ ይሆናል፡፡

ሰንጠረዥ 10
የውጭ ክፍያ ሚዛን
(በሚሊዮን ብር)

| | 1989 | 1990 | 1991 |
|---|---|---|---|
| ሀ. የእቃዎች ንግድ ሚዛን | -4613.7 | -5196.4 | -8065.7 |
| የወጪ ንግድ (ኤፍ ኦ ቢ) | 3891.5 | 4141.6 | 3636.3 |
| ቡና | 2307.4 | 2889.5 | 2112.7 |
| ሌሎች | 1584.1 | 1252.1 | 1523.6 |
| የገቢ ንግድ | -8505.2 | -9338.0 | -11702.0 |
| ነዳጅ | -1568.5 | -2282.8 | -1329.9 |
| ሌሎች | -6936.7 | -7055.2 | -10372.1 |
| ለ. አግልጋሎት (የተጣራ) | 653.4 | 656.0 | 622.4 |
| ሐ. የተጣራ የእቃዎችና የአገልግሎት ክፍያ | -3969.3 | -4540.4 | -7443.3 |
| መ. ከግል የተዛወረ ገቢ (የተጣራ) | 1677.7 | 2180.3 | 2171.9 |
| ሠ. የዘመኑ ሂሣብ ሚዛን | -2282.6 | -2360.1 | -5271.4 |
| ረ. የግል ካልሆኑ ምንጮች የተዛወረ ገቢ (የተጣራ) | 1469.7 | 1793.6 | 1598.9 |
| ሰ. ከውጭ ብድር (የተጣራ) | -1025.7 | 595.2 | 1739.6 |
| የረጅም ዘመን (የተጣራ) | -963.9 | 174.0 | 1675.0 |
| የአጭር ጊዝ (የተጣራ) | -61.8 | 421.2 | 64.6 |
| ሸ. ግድፈትና ወይም ያልተገለጸ | -714.6 | -183.8 | 1580.0 |
| ቀ. አጠቃላይ ሚዛን | -2553.2 | -155.1 | -352.9 |
| የጉድለት አሸፋፈን | | | |
| በ. የተከፈለ | 2553.2 | 155.1 | 352.9 |
| ተ. ከገንዘብ ባለሥልጣናት | 1777.8 | -205.4 | -256.9 |
| ቸ. ያልተከፈለ እዳ | 762.9 | 360.5 | 318.4 |
| ኀ. የእዳ ክፍያ እርዳታ | 12.5 | 0.0 | 290.4 |
| ነ. የተሰረዘ | 12.5 | 0.0 | 219.3 |
| ኘ. ክፍያው የተራዘመ | 0.0 | 0.0 | 72.1 |

ምንጭ፡- ብሄራዊ ባንክ፡፡

እንደምሳሌ አድርገን የምንመለከተው የ1991ን የክፍያ ሚዛን ነው:: የሰንጠረዡ የመጀመሪያ ረድፍ የእቃዎችን ሚዛን ያሳያል:: ይህም ማለት ወደ ውጭ ለሸጥነው እቃ በተከፈለንና ከውጭ ላስገባነው እቃ በከፈልነው መካከል ያለውን ሚዛን ነው::

በ1991 ዓ/ምህረት 3.6 ቢሊዮን የማያወጣ እቃ ሸጠን የ 11.7 ቢሊዮን ብር እቃ ገዛን:: የገዛነው ከሸጥነው በ 8.1 ቢሊዮን ብር ብልጫ አለው ማለት ነው:: ይህም የአገር ውስጥ ፍላጎትና አቅርቦት ወይም ገቢና ወጪ ነጸብራቅ ነው:: ይህ በጣም ጎጂ ነው::

መስመር (ለ) ላይ የተካተተው ከአገልግሎት የተገኘ የተጣራ ገቢ ነው:: ይህም ማለት የገዛነው ከሸጥነው ተቀንሶ ማለት ነው:: በ1991 ዓ/ምህረት ከአገልግሎት የሸጥነው ከገዛነው በ622 ሚሊዮን ብር በልጧል:: ይሄ በጣም ጥሩ ነው::

መስመር (ሐ) የእቃዎችንና የአገልግሎት አጠቃላይ ሚዛን ይሰጣል:: የሁለቱ ሲደመር ጉድለት ወደ 7.4 ቢሊዮን ብር ዝቅ ብሏል::

መስመር (መ) ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች የላኩት ገንዘብ ወይም ዕቃ ኢትዮጵያውያን እንዲሁ በርዳታ በስጦታ መልክ ወደ ውጭ ከላኩት ተቀንሶ የተገኘ የተጣራ ሂሳብ ነው:: እዚህም ላይ 2.2 ቢሊዮን ብር የሚሆን ጠቀም ያለ ገቢ ተገኝቷል::

መስመር (ሠ) በዚያን አመት ያካሄድነውን ሚዛን ያሳያል:: ይህ ሚዛን እጅግ ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም አጠቃላይ የውጭ ሁኔታችንን ሲለሚያሳየን:: በዚህ መስመር ላይ ለ 1991 ዓ/ምህረት የምናየው የ 5.3 ቢሊዮን ጉድለት ነው:: ይህም መከፈል አለበት::

ይህን ጉድለት መሸፈኛ የምንጠቀመው ዕርዳታና ብድር ናቸው:: በመሆኑም ሁለቱንም ፍለጋ መሄድ አለብን ማለት ነው:: በዚህ አመት የግል ካልሆኑ ድርጅቶች የ 1.6 ቢሊዮን ብር ዕርዳታ አገኘን (መስመር ረ):: በዚህም ላይ 1.7 ቢሊዮን ብር ብድር ተበደርን (መስመር ሰ):: ይህንን ሁሉ ጨምሮ ብሄራዊ ባንክ ሂሳቡን ሲሰራ የ 1.6 ቢሊዮን ብር ገቢ አገኘ (መስመር ሸ)::

ይህ ሁሉ ሂሳብ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ከተወራረደ በኋላ አጠቃላይ ሚዛኑ (መስመር ቀ) የ 353 ሚሊዮን ብር ጉድለት ያሳያል:: ከዚህ ውስጥ 318 ሚሊዮን ብር በዘመኑ መከፈል ከነበረበት የውጭ ብድር ያልተከፈለው ነው:: የ 290 ሚሊዮን ብር እዳ ሲሰረዝልን ለ 72 ሚሊዮን ደግሞ የክፍያው ጊዜ ተራዘመልን::

በአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (ገቢችንና)ና የአገር ውስጥ ወጪ ስንነጋገር አንዱ በአፅንኦት ያየነው ፋይዳ ከገቢአችን ከወጪአችን መብለጡን ነው:: ይህም በክፍያ ሚዛናችን በቅጡ ተንፀባርቋል::

## የውጭ ዕዳ

የውጭ ንግድ ይዞታችን እንደሚያሳየው ከምንሸጠው የምንገዛው ዕጅግ የናረ ነው። በአጭር ጊዜ ሊደረግ የሚችለው ብድርና እርዳታን መፈለግ ነው።

ካለፉት አመታት የተከማቸ ብድር በአሁኑ ጊዜ ወደ 5.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ብር የውጭ እዳ ተሸክመናል። በመንግስት ያላሰለሰ ጥረት የመስኮቦች መሳሪያ እዳ ባይቀነስ ኖሮ የውጭ እዳው ወደ 11 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በደረሰ ነበር።

በ 1991 ዓ/ምህረት መክፈል ከነበረብን 1.1 ቢሊዮን ብር ዋናና የ 457 ሚሊዮን ብር ወለድ በድምሩ የ 1.6 ቢሊዮን ብር ውስጥ የከፈልነው 954 ሚሊዮን ብር ብቻ ነው።

ይውጭ እዳ መዘዙ ብዙ ነው። ዕዳ ለመክፈል የአገርን ጥቅም መስዋዕት ማድረግ ይኖራል። በያመቱ ከምትገኝ ትንሽ የውጭ ምንዛሬ ተቀንሶ ለእዳ ክፍያ መሄድ አለበት። ይህም ሲደረግ መሃይምነትን ለመቀነስ፣ የታመሙትን ለማሳከም፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ለህዝብ ለማቅረብ፣ መንገድ ለመስራት፣ ወዘተ ለንጠቀምበት የምንችለውን የውጭ ምንዛሬ እናጣለን ማለት ነው። ይህ እንግዲህ የምንከፍለውን የሚመለከት ነው።

መክፍል ያቃተንን ማሩን ወይም ጊዜ ስጡን በሚባልበት ጊዜ አበዳሪ አገሮች በአለም ባንክና በአልም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አማካይነት ለኛ አገር የማይበጅና የማይጠቅም፣ ግን የበለጸጉ አገሮችን ጥቅም የሚያራምድና የሚያስጠብቅ መርሀግብር ተግባራዊ እንድናደርግ ስገድዱናል።

ከዚህ የሚከተለው ጉዳይና የልማት አቅጣጫችን ይህንን የውጭ ጫና ሚቀንስበትን መሆን ይኖርበታል። ለዚህም ወደ ውጭ የምንሸጠውን አበራክተን ከውጭ ምንሸምተውን መቀነስ ይኖርብናል። ይህንን እስካላደረግን ድረስ ከውጭ ጫና ለመገላገልና ነፃነታችንን አስከብረን ለመኖር አንችልም.

## XI. የመስተዳድሩ ወጭና ገቢ

በዚህ አርዕስተ ጉዳይ ሰፋ ያለ መግለጫና ጽሁፍ ከሌላ ሰው ስለምታገኙ እዚህ መሰረታዊውን ጉዳይ ብቻ እነሳለሁ:: የመስተዳድሩ የወጪና የገቢ መርሃግብር ላአገር ልማት እጅግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል:: እንኳን እንደኛ አይነቱ ደሃ አገር ይቅርና በበለጸጉተ አገሮችም ቢሆን ያለመስተዳደሩ ተሳትፎና እገዛ የኢኮኖሚ ስክንትና እድገት የተፈለገውን ያህል ሊሆን አይችልም:: ይህንን ለመገንዘብ የመስተዳድሩ በጀት ግብ ምንና እንዴት እንደሆን ጠቅሰል ያለ ገለጻ ያስፈልጋል::

መንግስት በበጀት (በዚህ ወረቀት የበጀትን ፅንሰሃሳብ ሰፋ በማድረግ የመስተዳደሩን የገቢና የወጪ መርሃግብር ወይም በፈረንጆቹ Fiscal Policy ለሚባለው ተጠቅመንበታል) መርሃግብሩ ለማድረግ የሚችለው ብዙ ነው:: መሰረታዊው ኢላማው የስክና ቀጣይነት ያለው ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገትን እውን ማድረግ ነው:: ሌላ አላማው የውጭ የክፍያ ሚዛን እንዳይዛባና ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና እንዳይፈጠርብን ማድረግ ነው:: ሌላው አላማ የዋጋ መረጋጋትን ማስፈን ነው:: ሌላው የአገሩ ህዝብ በስራ እጥነት እንዳይቸገር የስራ እድል በሰፊው መፍጠሪያ መሣሪያ ነው:: ሥራ እጥ ሲበዛ አገሪቷ እነዚህ ሰዎች ቢሰሩ የሚገኘውን ምርት ማጣት ብቻ ሳይሆን ሰላምና መረጋጋትንም የሚያውክና ወንጀልን የሚያበራክት ሁኔታ ይፈጥራል:: እነዚህን ግቦች ከሚያሟላባቸው መሳሪያዎች አንዱ በጀት ነው::

በጀት አንድ መስተዳደር የገጠርና የከተማን፣ የኢንዱስትሪንና የግብርናን፣ የትናንሽ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ ፋብሪካ ግንባታ ምርጫ የሚገልጥበትና ትግባራዊ የሚያደረግበት፣ በአጠቃላይ በአገሩ ውስጥ የሚካሄደውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ስፋት፣ ጥልቀትና ፍጥነት፣ የማህበራዊ ልማት ማለትም እንደትምህርት ጤና መገናኛ መስፋፋት ወዘተ፣ ሊገድብ ወይም ሊያስፋፋ የሚችልበት መሳሪያና ዘዴ ነው::

በመሆኑም ድህነትን ለመቀነስ፣ አገርን ለማልማት፣ የህብረተሰብን የኑሮ ደረጃ በቀጣይነት ለማሻሻል የሚያስችል ትልቅ መሣሪያ የመስተዳደሩ የበጀት መርሃግብር ነው::

ምስተዳደሩ እነዚህን አላማዎች ለሟሟላት የሚችለው የበጀቱን የገቢና የወጪ መርሃግብር በመጠቀም ነው::

### የመስተዳድር ገቢ

መስተዳድሩ ገቢ የሚሰበስበው ከአላም አንጻር ነው:: አንዱ አላማው ወጪውን ለመሸፈን የሚስፈልገውን ገንዘብ ለማሰባሰብ ነው:: ገቢን የሚያሰባስበው ግብርና ቀረጥ በመጣል ነው:: ሆኖም ቀረጥና ግብር በሚጣልበት ጊዜ ምስተዳደሩ ማሰብ ያለበት ገቢውን በማሳደጉ ላይ ብቻ ሳይሆን ለዚህ ጉዳይ የሚጣለው ግብርና ቀረጥ በአይነትም ሆነ በከፍተኛነት በግብርና ቀረጥ ከፋዩ

ላይ ብሎም በኢኮኖሚውና ማህበራዊው ልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ጎጂ ተጽእና እንዳያሳድር ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

ግብር ባገር ውስጥ በገቢና በሸቀጦች ላይ የሚጣል ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ በህዝበ ላይ ተፅእኖ ማሳደራቸው የታወቀ ነው፡፡ የገቢ ግብር በሚወሰንበት ጊዜ መታሰብ ያለበት ምን ያህለ ከማን ላይ የሚለው ነው፡፡ እጅግ የናረ የገቢ ግብር ለትጋትና ለቀልጣፋ ሥራ እንቅፋት ነው፡፡ ብዙ አግኝቼ መስተዳደሩ የሚወስደው ከሆነ ለምን እሰራለሁ ብሉ ይሰነሰፋል፡፡ አለበለዚያም ገቢውን በመደበቅ ወይም በጉቦ በህጉ መሰረት መከፈል የሚገባውን ግብር ሳይከፍል ያመልጣል፡፡

ግብሩ በጣም ዝቅ ያለ እንደሆን የመንግስት ገቢ ከመቀነሱም ሌላ ፍትሃዊ የገቢ መከፋፈል መርህም ይጣሳል፡፡ ምክንያቱም ከፍ ያለ ገቢ የሚያገኙ ሰዎች ትንሽ ግብር ስለሚከፍሉ፡፡

በውጭ ንግድ ላይ የሚጣለውም ታክስ እንዲሁ የተለያየ ኢላማ ለመምታት ያስችላል፡፡ የውጭ ክፍያ ሚዛንን ጤናማ አቅጣጫ ለማስያዝ በገቢ ንግድ ላይ በተለይም በቅንጦት ሸቀጦች ላይ ከፍ ያለ ታክስ ሊጣል ይችላል፡፡ በአንፃሩም የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን አቅማቸውን አደርጅተው ብቃታቸውን አጎልብተው በአገር ውስጥ ገበያ ብቁ ተፎካካሪ እስኪሆኑ መስተዳድሩ ድጋፍ ከሚያደርግበት መሳሪያዎች አንዱ ያገር ውስጥ አምራቾችን የሚወዳደሩ የውጭ ሸቀጦች ላይ ከፍ ያለ ታሪፍ መጣል ነው፡፡

መዋእለ ነዋያቸውን በልማት ሥራ ለሚያውሉ ሰዎች መስተዳድሩ ከውጭ ለሚያስመጧቸው ቁሳቁሶች ከታክስ ነፃ ማድረግ ከመቻሉም ሌላ ለተወሰነ ጊዜ ከታክስ ከገቢ ግብር ነፃ ያደርጋቸዋል፡፡

## የመስተዳድሩ ወጪ

የወጪ በጀት አደላደል የመስተዳድሩ እምነትና ሃሳብ በይፋ የሚያሳይ ነው፡፡ የፖለቲካ መሪዎች ብዙ ጊዜ ይጎንን ያንን እናደርግላችኋለን እያሉ ቃል ይገባሉ፡፡ ቃላቸውን ለማክበራቸው ፈተናው የወጫአቸው ዝርዝር ነው፡፡

መስተዳድሩ ሊያደርግ የሚፈልገው ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ ኢኮኖሚን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ መሰረተልማቶችን መዘርጋት፣ የማመረቻ አቅምን መገንባት፣ የግሉ ክፍል ተጠናክሮ የኢኮኖሚውን እንቅስቃሴ እንዲያነለብት አስፈላጊውን እንያደርግ ማገዝና ማበረታታት ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡

ኢኮኖሚ ዕንሰ ሃሳብና የድህነት ቅነሳ

ሆኖም ግን መስተዳደሩ የሚፈለገውን ሁሉን ለማድረግ አቅሙ ስለሌለው መደረግ ከሚገባቸው መሃል ቅደም ተከተል አውጥቶ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት የወጪ በጀት ይመድባል፡፡ በመሆኑም መስተዳድሩ ከሁሉ የበለጠ ችግር ነው፣ ወይም አንድን ችግር ለመፍታት ቁልፍ ነው ብሎ ትኩረት ለሰጠባቸው ተግባራት በጀት በመመደብ ተግባራዊ ያደርጋቸዋል፡፡

በመሆኑም መንገድ የሚሰራው፣ ትምህርት ቤቶችና የህክምና ተቋማት የሚገነቡት፣ ወዘተ ይህንን መሰረት በማድረግ ነው፡፡